# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የፕላስቲክ ምርቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**ማውጫ**


**የአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ** ........ 1

**ክፍል አንድ** ........ 4

**መግቢያ** ........ 4

የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አመሰራረት ........ 4

የባለስልጣኑ ራእይ ፣ ተልዕኮ እና ሥልጣንና ተግባር ........ 5

ራዕይ፡- ........ 5

ተልዕኮ፡- ........ 5

የባለስልጣኑ ስልጣንና ተግባር፡- ........ 5

የባለስልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል ........ 7

ድርጅታዊ መዋቅር ........ 7

የሰው ኃይል ........ 8

የባለስልጣኑ የፋይናንስ ምንጭ ........ 8

ሀ) መደበኛ በጀት ........ 8

ለ) ከካፒታል (የፕሮጀክት ማስፈፀሚያ) በጀት ........ 9

የኦዲቱ አላማ ........ 9

የኦዲት አካባቢ ........ 9

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 9

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ........ 10

የአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ........ 10

የአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ ወሰን ........ 10

የኦዲቱ ዘዴ ........ 10

የደረቅና አደገኛ ቆሻሻ ህግ ተከባሪነትና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት የስራ ሂደት መግለጫ /System Description/ ........ 10

**ክፍል ሁለት** ........ 11

**የኦዲት ግኝቶች** ........ 11

የደረቅ ቆሻሻ የህግ ማዕቀፎች ተዘጋጀተው ተግባራዊ ስለመደረጋቸው፡ ........ 11

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህጎችና ደረጃዎች ተፈጻሚነት በተመለከተ፡ ........ 14

የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ፈቃድን በተመለከተ፡ ........ 16

የፕላስቲክ አምራች ተቋማት ክትትል በተመለከተ፡ ....21
የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ የፕላስቲክ ምርቶችን በሌሎች ተተኪ ምርቶች ስለመለወጥ እና የፕላስቲክ አምራቾች ምርቶቻቸውን ስለመሰብሰብ፡ ....24
የፕላስቲክ ቆሻሻ የሚያደርሰው ጉዳት ጥናት እና የአካባቢ አያያዝ ግንዛቤ ማስፋፊያን በተመለከተ፡ ....25
የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ስለመዘጋጀታቸው፡ ....27
የቆሻሻ አሰባሰብ፣ የማጓጓዣ ጊዜና ምልልስ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ እና ቋሚ ስለመሆኑ፡ ....29
ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ሊደርስ የሚችል ብክለትን የመከላከያ እርምጃ መውሰዱን ክትትል ስለመደረጉ፡ ....30
በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች የጤንነትና ደህንነት መጠበቂያ በተመለከተ ....36
የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ቁጥጥር በማድረግ እርምት እርምጃ ስለመውሰዱ፡ ....37
የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና የፕላስቲክ አምራች ፈቃድ አሰጣጥ በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት ስለመዘርጋቱ፡ .38
በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት መስክ ኢንቨስትመንት ስለመስፋፋቱ፡ ....39
በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ ስልጠና ስለመሰጠቱ፡ ....41
በደረቅ ቆሻሻና ፕላስቲክ ምርቶች ዙሪያ ዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን በመውሰድ ተግባራዊ ስለመደረጋቸው፡ ....42
**ክፍል ሶስት** ....44
***መደምደሚያ*** ....44
**ክፍል አራት** ....47
***የማሻሻያ ሃሳቦች*** ....47
**አባሪ- 1** .... ii
***የአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ተቋማዊ መዋቅር*** .... ii
.... ii
አባሪ 2 ....1
የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) ....1
አባሪ 3 ....6
በዝርዝር ኦዲቱ ወቅት የተዳሰሱ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ....6
አባሪ- 4 የደረቅና አደገኛ ቆሻሻ ህግ ተከባሪነት ዳ/ሬት የስራ ሂዳት ስዕላዊ መግለጫ፡- ....1

## የአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ

በሀገራችን አሁን ያለው የከተሞች መስፋፋትና የህዝብ ቁጥር መጨመር የደረቅ ቆሻሻ የምንጨታ ምጣኔ እንደሚጨምር ይታወቃል፡፡ ከተሞችም ብዙ ህዝብ አንድ ላይ ተጠጋግቶ የሚኖርባቸው ቦታዎች በመሆናቸው እና ከፍተኛ መጠን ያለው ቆሻሻ የሚፈጠርና የሚከማች በመሆኑ ከንጽህና ጉድለት በሚመጡ የተለያዩ በሽታዎች የተጋለጡ ናቸው፡፡

ከደረቅ ቆሻሻዎች መካከል የፕላስቲክ ቆሻሻ አንዱ ሲሆን፤ ለተለያዩ በርካታ አገልግሎቶች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ በመሆኑና በቀላሉ የማይበሰብስ፣ሲቃጠልም የአየር ብክለት የሚያስከትል በመሆኑ አካባቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ግንባር ቀደም እየሆነ መጥቷል፡፡

የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ሁሉም ኢትዮጲያዊ ንፁንና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው ጥረት ማድረግ እና ማንኛውም ኢኮኖሚያዊ ልማት የአካባቢ ደህንነት የሚያናጋ መሆን እንደሌለበት እንዲሁም ማንኛውም ሰው ጤናማና ንፁህ አካባቢ የመኖር መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ይህንን መብትና ግዴታ ለማስከበር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 9/1987 ራሱን ችሎ በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ ተቋቋመ፤ በአሁን ወቅትም የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር1263/2014 መሰረት እየሰራ ይገኛል፡፡ ይህንኑ ስልጣንና ኃላፊነቱን መወጣቱን ለማረጋገጥ መ/ቤታችን የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት አከናውኗል፡፡

የአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የፕላስቲክ ምርቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነትን ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን እና የችግሮቹን መንስኤ በመለየት የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ ነው፡፡

ለአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ የተመረጡት የትኩረት አቅጣጫዎች፡ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና ቁጥጥርን በተመለከተ ባለስልጣኑ በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል ህግና ስርዓት በማዘጋጀት ተግባራዊ ስለማድረጉ መገምገም፤ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ ቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነትን መገምገም እና ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣አጓጓዝ፣ አወጋገድ በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲቱ የተከናወነው በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እና ሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመከለስ፣ የመስክ ምልከታ በማድረግ እና መረጃዎችን በመተንተን ነው፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፉ እና በኢትዮጵያ የክዋኔ የኦዲት ስታንዳርድ እንዲሁም ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2011 እስከ 2015 ዓ.ም የአንደኛው ሩብ ዓመት ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

በኦዲቱ ወቅት የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የፕላስቲክ ምርቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ ያለው አፈፃፀም ላይ የሚከተሉት ክፍተቶች ታይተዋል፡-

- ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999 በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ደንቦች እና መመሪያዎች አላዘጋጀም፤ ይህን አዋጅ ለማሻሻል (በ2012 ዓ.ም) እንዲሁም በ1989 ዓ.ም የወጣውን የአካባቢ ፖሊሲን ለማሻሻል (በ2013 ዓ.ም) በረቂቅ ደረጃ ያዘጋጀና ለሚመለከታቸው አካላት ያቀረበ ቢሆንም ፀድቆ ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትል አላደረገም፡፡
- ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ሊደርስ የሚችል ብክለትን የመከላከያ እርምጃ እንዲወስዱ እና ዘመናዊ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንዲኖር ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትልና ድጋፍ አላደረገም፡፡
- ባለስልጣኑ ማንኛውም ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል የልማት ፕሮጀክቶች ባለቤት ወደ ትግበራ ከመግባቱ በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ በማካሄድ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ፈቃድ ማግኘቱን እንዲሁም በሚመለከታቸው የዘርፍ መ/ቤቶች የተሰጡ የአካባቢና የማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ የይሁንታ ፈቃዶች በህጉ መሠረት እየተገበሩ መሆናቸውን አላረጋገጠም፡፡
- ባለስልጣኑ ውፍረታቸው 0.03 ሚሊ ሜትርና ከዚያ በታች ሆነው በስብሰው ከአፈር ጋር የማይዋሃዱ የፕላስቲክ ምርቶችን ተለይቶ ለተገለፀ አገልግሎት በቀር ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም በአገር ውስጥ እንዳይመረቱ ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትል በማድረግ ዘገባ አላዘጋጀም፤ ባደረጋቸው ክትትሎች ከህግ ውጪ ሰርተው በተገኙ ድርጅቶች ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እርምጃ እንዲወሰድ አላደረገም።
- ባለስልጣኑ የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ የፕላስቲክ ምርቶችን የሚያመርቱ አምራቾች በጊዜ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ምርቱን የሚያቋርጡበትን እና በሌሎች ተተኪ ምርቶች የሚለውጡበትን እንዲሁም ያመረትዋቸው ምርቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ የሚሰበስቡበትና መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉበት አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት በተመለከተ ከዘርፉ መ/ቤቶች፣ ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም ፤የከተማ አስተዳደሮች እና ክልሎች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህግ ተከባሪነት ደረጃን የሚገልፅ የቁጥጥርና ክትትል ሪፖርት መዘጋጀቱን ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ አላደረገም፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች መፍትሄ ሊሆን የሚችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

- ባለስልጣኑ በረቂቅ ደረጃ ያዘጋጃቸውን በ1989 ዓ.ም የወጣውን የአካባቢ ፖሊሲን ማሻሻያ እና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999 ማሻሻያ በሚመለከታቸው አካላት እንዲፀድቁ ክትትል በማድረግ ማፀደቅ አለበት፤ ተሻሽሎ የሚወጣውን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ

የሚያስፈልጉ ደንቦች እና መመሪያዎች በማዘጋጀት እና ክትትል አድርጎ በማፀደቅ የህግ ማዕቀፎችን ሊያዘጋጅና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ በማድረግ ለስራ አፈፃፀም ትግበራ ምቹ ማድረግ አለበት፡፡

- ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ሊደርስ የሚችል ብክለትን የመከላከያ እርምጃ መወሰዱን ክትትል በማድረግ፡ ምልክት የተደረገባቸው ጉድፍ ማጠራቀሚያዎች በየጎዳናው ዳርና በሌሎች የሕዝብ ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲቀመጡ፤ቆሻሻ በሚሰበሰብበት ወቅት ቢያንስ 2 የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ማለትም የሚበሰብስ እና ሊበሰብስ የማይችል ቆሻሻን ማጠራቀም የሚያስችል የተለያየ ከለር ባለው ገንዳ እየተከማቸ ስለመሆኑ፤ የጉድፍ ማጠራቀሚያ ሞልቶ ሳይዝረከረክ ቆሻሻ በየወቅቱ በቆሻሻ ሰብሳቢ ተሽከርካሪዎች መነሳቱን ማረጋገጣቸውን እና ዘመናዊ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ስለማዘጋጀታቸው ክትትል እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል::
- ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ፕላስቲክ አምራቾችን እና የቆሻሻ ማከማቻ ላንድ ፊል ፕሮጀክቶች ጨምሮ ማንኛውም ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል የልማት ፕሮጀክቶት ባለቤት ወደ ትግበራ ከመግባቱ በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ በማካሄድ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ፈቃድ አግኝቶ ወደ ስራ እንዲገቡ ሊያረግ እንዲሁም በተሰጣቸው ፈቃድ መሰረት መስራታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ ፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች ክትትል በዓመታዊ እቅዱ ላይ በማካተት ፕላስቲክ አምራች ድርጅቶችን አዋጁ ላይ በተቀመጠው ህግ መሰረት ማምረታቸውን እንዲሁም ከውጭ አገር ለሚገቡ የፕላስቲክ ምርቶች ተለይተው ለተፈቀዱ ምርቶች ብቻ መግባታቸውን ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትል አድርጎ ዘገባ በማዘጋጀት ህግን በተላለፉት ላይ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ የፕላስቲክ አምራች ተቋማት ያመረትዋቸው ምርቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ የሚሰበስቡበትና መልሰው ጥቅም ላይ የሚያውሉበት እና የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ የፕላስቲክ ምርቶችን የሚያመርቱ አምራቾች በጊዜ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ምርቱን የሚያቋርጡበትን እና በሌሎች ተተኪ ምርቶች የሚለውጡበትን አሰራር በህግ ማዕቀፍ እንዲደገፉ በማድረግ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እንዲሁም የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ቅንጅታዊ አሰራሩን ሊያጠናክር እንዲሁም የከተማ አስተዳደሮች እና ክልሎች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህግ ተከባሪነት ደረጃን የሚገልፅ የቁጥጥርና ክትትል ሪፖርት መዘጋጀቱን ሊከታተል ፣ ሊቆጣጣር እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

የሚሉት ይገኙበታል፡፡

# ክፍል አንድ

***መግቢያ***

1. *ደረቅ ቆሻሻ ማለት፤ የማይፈለግ ተብሎ የተጣለ ማንኛውም ፈሳሽ ወይም ነፋሽ ያልሆነ (በንፋስ የማይንቀሳቀስ) ነገር ነው፡፡*
2. *በሀገራችን አሁን ያለው የከተሞች መስፋፋትና የህዝብ ቁጥር መጨመር የደረቅ ቆሻሻ የምንጨታ ምጣኔ እንደሚጨምር ይታወቃል፡፡ ከተሞችም ብዙ ህዝብ አንድ ላይ ተጠጋግቶ የሚኖርባቸው ቦታዎች በመሆናቸው እና ከፍተኛ መጠን ያለው ቆሻሻ የሚፈጠርና የሚከማች በመሆኑ ከንጽህና ጉድለት በሚመጡ የተለያዩ በሽታዎች የተጋለጡ ናቸው፡፡*
3. *በኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ ካሉት ዋና ዋና የአካባቢ ጥበቃ ችግሮች መካካል አንዱ የደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ አለመያዝ እና አለመወገድ ሲሆን በዚህም የተነሳ ቆሻሻ የተለያዩ ቦታዎች ተዝረክርኮ ለጤና ጎጂ ለሆኑ ተዋሲያን መራቢያ አመቺ ቦታ ከመፍጠሩም በተጨማሪ  የአየር ንብረት ለውጥ ከሚያባብሱ ጉዳዮች ውስጥ አንዱና ተጠቃሽ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከከተሞቻችን የሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ የተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ችግሮችን እያስከተለ ይገኛል፡፡*
4. *ከደረቅ ቆሻሻዎች መካከል የፕላስቲክ ቆሻሻ አንዱ ሲሆን፤ ለተለያዩ በርካታ አገልግሎቶች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ በመሆኑና በቀላሉ የማይበሰብስ፤ ሲቃጠልም የአየር ብክለት የሚያስከትል በመሆኑ አካባቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ግንባር ቀደም እየሆነ መጥቷል፡፡*
5. *በዚህ ረገድ የከተሞችን ጽዳት በመጠበቅና ዘላቂ ልማት በማረጋገጥ፣ የህብረተሰቡን አኗኗር በመለወጥ፣ አመቺ የኑሮ ሁኔታንና ጤነኛ አምራች ዜጋ በመፍጠር ለልማታችን መፋጠን፣ የኢንቨስትመንትና ቱሪዝም መስዕብ እንዲስፋፋ በማገዝ ለሀገራችን ገጽታ ግንባታ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ከተሞቻችን ተገቢውን ጽዳት ይዘው ማደግ የሚችሉበትን ስርዓት መዘርጋት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡*

## ***የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አመሰራረት***

6. *የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ሁሉም ኢትዮጰያዊ ንፁንና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው ጥረት ማድረግ እና ማንኛውም ኢኮኖሚያዊ ልማት የአካባቢ ደህንነት የሚያናጋ መሆን እንደሌለበት እንዲሁም ማንኛውም ሰው ጤናማና ንፁህ አካባቢ የመኖር መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ይህንን መብትና ግዴታ ለማስከበር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 9/1987 ራሱን ችሎ በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ ተቋቋመ፡፡*
7. *በአንድ በኩል ለአካባቢ ልማትና አያያዝ የስራ እንቅስቃሴዎችን በሌላ በኩል ለአካባቢ ጥበቃ ቁጥጥር እና ክትትል ተግባራት የተለያዩ አካላት መስጠት የስራ ኃላፊነቶች አለመጣጣምንና የስራ ድግግሞሽን በማስወገድ በአካባቢያዊ ሀብቶች በዘላቂነት ለመጠቀም የሚረዳ በመሆኑ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ የአካባቢ ጥበቃ ማቋቋሚያ አዋጅ 295/1995 ዓ.ም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተብሎ ተቋቋመ፡፡*

8. የደን ልማትን ለማስፋፋትና አያያዙን ለማሻሻል ራሱን የቻለ ኃላፊነት የሚወስድ ተቋም በማስፈለጉ ሀምሌ 22/2005 ዓ.ም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ 691/2003 አንቀፅ 9 ላይ አዲስ ንኡስ አንቀፅ 21 በመጨመር በአዋጅ 803/2005 የፌደራል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣንና ከግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የደን ንኡስ ዘርፍን በማቀናጀት የአካባቢና የደን ሚኒስቴር እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡
9. በመቀጠልም ህዳር 29/2008 ዓ.ም የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን ያወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚስቴር ተብሎ ተቋቋመ::
10. እንዲሁም በ2011 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 ዓ.ም የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ተብሎ ተቋቋመ፡፡
11. በመጨረሻም በ2014 ዓ.ም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተብሎ እንዲጠራ ተወስኗል፡፡

## የባለስልጣኑ ራእይ ፣ ተልዕኮ እና ሥልጣንና ተግባር

**ራዕይ፡-**

12. ዘላቂ የአካባቢና የደን አያያዝ፣ ልማትና አጠቃቀምን በማረጋገጥ በ2017 ዓ.ም ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን የገነባች መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር ሆና ማየት፡፡

**ተልዕኮ፡-**

13. ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት የሚያስችሉ የአካባቢ ጥበቃና የደን ሃብት አያያዝ፣ ልማትና አጠቃቀም ለዘላቂ ልማትና ለድህነት ቅነሣ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የአካባቢ ሥርዓቶችን ማዘጋጀትና ተፈፃሚነታቸዉን ማረጋገጥ፣ ምርምርና የአረንጓዴ ቴክኖሎጂ ሽግግርን ማስተባበርና ማካሄድ፣ ትምህርትና ግንዛቤን ማስፋፋት፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ትግበራን በዘርፍ መ/ቤቶችና በክልሎች ማስተባበር፣ የተግባሪዎችን አቅም መገንባት፣ የደን ኢንቨስትመንትንና ግብይትን ማስፋፋት፣ ዓለም አቀፋዊ የአካባቢና የአየር ንብረት ድርድሮችንና ስምምነቶች ትግበራን የማስተባበር እና ወቅታዊ የአካባቢና የደን ሁኔታና ለውጥ ዘገባን ማዘጋጀትና ዉጤታማነት ማረጋገጥ ነው፡፡

**የባለስልጣኑ ስልጣንና ተግባር፡-**

14. የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተብሎ የተሰየመ ቢሆንም የአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን በነበረበት ወቅት የነበረውን የኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነት ለባለስልጣኑ የተሰጠ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት የኦዲት አካባቢውን በሚመለከት የሚከተሉት ዝርዝር ኃላፊነቶች ተሰጥቶታል::

- በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉት የአካባቢ ደህንነት ዓላማዎችና በአገሪቱ የአካባቢ ፖሊሲ የተመለከቱት መሠረታዊ መርሆዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ያስተባብራል፣
- በመንግሥትም ሆነ በግል የሚወጡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ሥልቶች፣ ሕጎችና መርህ ግብሮች እና ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ወይም ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ሥርዓቱ በተግባር ላይ መዋሉንም ይከታተላል፣
- በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ መሠረት ለልማት ፕሮጀክት እና ፕሮግራም የይሁንታ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የፕሮጀክቱ እና የፕሮግራሙ ትግበራ በአካባቢ ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ በሚመለከተው የዘርፍ የፈቃድ ሰጪ አካል ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ተገምግሞ ውሳኔ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፣
- ኢትዮጵያ ከተፈጥሮ ሃብቶች መሠረት፣ ከበረሃማነት፣ ከደን፣ ከአደገኛ ኬሚካሎች፣ ከኢንዱስትሪ ቆሻሻዎች እና ከሰው ሰራሽ የአካባቢ አደገኛ ንጥረ ነገሮች ጋር በተያያዘ ያፀደቀቻቸው አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የአካባቢ ስምምነቶችን በየዘርፉና በየአስተዳደር እርከኑ በሚተግበር ወቅት የድግግሞሽ፣ የሃብት ብክነትንና ክፍተትን ለማስቀረት የሚያስችሉ መርህ-ግብሮችን እና መመሪያዎችን ያዘጋጀል፣ መተግበራቸውንም ይከታተላል፣
- በዓለም አቀፍ የአካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነቶች ድርድር ላይ ይሳተፋል፣ በዘርፉ አገራዊ ምላሽን በማስተባበሩ በኩል ቁልፍ ሚና ይጫወታል፣ እንደአግባቡ ስምምነቶቹ እንዲፀድቁ ሃሳብ ያቀርባል፣
- ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍ የአካባቢ ውሎች ለመተግበር ተፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎችን፣ ስልቶችን፣ ሕጎችንና መርህ-ግብሮችን እንደሁኔታው ያዘጋጀል ወይም እንዲዘጋጁ ሃሳብ ያመነጫል፣ አዘገጃጀታቸውን ያስተባብራል፣ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣
- በልማት ዕቅዶችና በኢንቨስትመንት መርህ-ግብሮች ውስጥ የሚካተቱ የአካባቢ አዋጪነት ማስሊያ ቀመሮችንና የስሌት ሥርዓቶችን ያዘጋጀል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል ፣ እንደሁኔታውም በጥቅም ላይ የመዋላቸውን ሂደት ይከታተላል፣
- ዘላቂነት የጎደለው የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ልምድን፣ የአካባቢ ጉስቁልናን ወይም ብክለትን ለመከላከል በሚያስችሉ የመግቻ እርምጃዎች ወይም የማበረታቻ ዘዴዎች መጠቀምን በተመለከተ ሃሳብ ያቀርባል፣
- የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓትን ይዘረጋል፣
- የሀገሪቱን የአካባቢና የደን እንዲሁም ለአየር ንብረት ለዉጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በሚመለከት ዘገባን በየወቅቱ እያዘጋጀ ያሰራጫል፣
- መደበኛ ያልሆኑ የአካባቢ ትምህርት መርሃ- ግብሮችን ያስፋፋል፣ ትምህርቱን ይሰጣል፣ የአካባቢ ጉዳዮችን በመደበኛ ትምህርት ሥርዓት-

ትምህርት ውስጥ ለማካተት አግባብ ካላቸው መስሪያቤቶች ጋር ትብብር ያደርጋል፡፡

15.እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999 ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦችን በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ መመሪያዎች የማውጣት ኃላፊነት ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም፡

- ➢ ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ዝቅተኛውን የአስተዳደር እርከናቸውንና የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ ባሳተፈ መልኩ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀታቸውንና ተግባራዊ ማድረጋቸውን ይከታተላል፣
- ➢ እያንዳንዱ ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ዘገባ ማዘጋጀቱን ባለስልጣኑ ይከታተላል፣
- ➢ ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ሊደርስ የሚችል ብክለትን የመከላከያ እርምጃ መወሰዱን ይከታተላል፣
- ➢ ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ምልክት የተደረገባቸው ጉድፍ ማጠራቀሚያዎች በየጎዳናው ዳርና በሌሎች የሕዝብ ማዘውተሪያ ስፍራዎች መቀመጥቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑ ይከታተላል፣
- ➢ ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች የጉድፍ ማጠራቀሚያ ሞልቶ ሳይዝረከረክ ቆሻሻ በየወቅቱ መነሳቱን ማረጋገጣቸውን ክትትል በማድረግ እርምጃ ይወስዳል፣
- ➢ ባለስልጣኑ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር አግባብነት ያለው የፌደራል የአካባቢ ደረጃ በመከተል የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንዲገነባና አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረጋቸውን ይከታተላል፣
- ➢ ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ከረጢት ውፍረቱ 0.03 ሚ.ሊ ሜትር እና 0.03 ሚ.ሊ ሜትር በታችም ሆኖ በስብሶ ከአፈር ጋር የማይሃድ የፕላስቲክ ከረጢት የማምረት ወይም ወደ ሃገር ውጥ የማስገባት ፈቃድ እንዳይሰጥ ይከለክላል፣
- ➢ ባለስልጣኑ ውፍረቱ 0.03 ሚ.ሊ ሜትር እና 0.03 ሚ.ሊ ሜትር የሚንስ ሆኖ በስብሶ ከአፈር ጋር የማይዋሃድ የፕላስቲክ ከረጢት ተለይቶ ለተገለፀ አገልግሎት ብቻ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ወይም በአገር ውስጥ እንዲመረት የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡
- ➢ ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት መስክ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውን ይከታላል፣ይደግፋል እና
- ➢ ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች የአካባቢ ግንዛቤ ማስፋፊያ ተግባራትን ማቀዳቸውን እና መተግበራቸውን ይከታተላል

የሚሉ ናቸው፡፡

## የባለስልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

16.የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን 2 የዋና ዳይሬክተሩ አማካሪዎች፣ የዋና ዳይሬክተር ፅ/ቤት ሃላፊ፣ 2 ም/ዋና ዳይሬክተሮች፣ 1 የአካባቢ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር አማካሪ፣ 3 ዳይሬክተር ጀኔራሎች እንዲሁም ከስራቸው

ባሉ 24 ዳይሬክቶሬቶች በተዋቀሩ የሥራ ክፍሎች የተደራጀ ተጠሪነቱም ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር ነው፡፡ (የአዲሱን የድርጅቱ መዋቅር ስዕላዊ መግለጫ ማስረጃ ተጠይቆ ያልቀረበልን ሲሆን የቀድሞውን የድርጅቱ መዋቅር ስዕላዊ መግለጫ ዝርዝር **በአባሪ 1** ተያይዘዋል፡፡)

**የሰው ኃይል**

17.ባለስልጣኑ በሕዳር ወር 2015 ዓ.ም ከቀረበው ማስረጃ ለማወቅ እንደተቻለው 118(44.1%)ሴት ሰራተኞች፣ 149(55.8%) ወንድ ሰራተኞች በድምሩ 267 ቋሚ ሰራተኞች ያሉ ሲሆን ባላቸው የሙያ ደረጃ ሲተነተን ፒ.ኤች.ዲ 1(0.37) ሁለተኛ ዲግሪ 59(22%) የመጀመሪያ ዲግሪ 111(41.5%) ዲፕሎማ 24(8.98%) ከዲፕሎማ በታች 72(26.9%) ናቸው፡፡ ለባለስልጣኑ የተፈቀደ የስራ መደብ ብዛት 477 ሲሆን አሁን ያለው 267 (55.9%) እና ክፍት ቦታ 210(44.%)ነው፡፡

| **የትምህርት ደረጃ** | **ወንድ** | **ሴት** | **ድምር** |
|---|---|---|---|
| ፒኤችዲ | 1 | - | 1 |
| ማስተርስ/ሁለተኛ ዲግሪ | 46 | 13 | 59 |
| የመጀመሪያ ዲግሪ | 70 | 41 | 111 |
| ዲፕሎማ/ቴክኒክናሙያ | 7 | 17 | 24 |
| ሌላ | 25 | 47 | 72 |
| **ድምር** | **149** | **118** | **267** |

**የባለስልጣኑ የፋይናንስ ምንጭ**

18.የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት መደበኛ እና ካፒታል በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2012-2015 ዓ.ም ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

**ሀ) መደበኛ በጀት**

| ዓ.ም | የተመደበ መደበኛ በጀት | በስራ ላይ የዋለ ወጪ | የወጣ ወጪ በፐርሰንት | ምርመር |
|---|---|---|---|---|
| 2012 | 272,009,319.34 | 221,386,242.88 | 81.4 | - |
| 2013 | 274,588,047.10 | 190,239,487.81 | 69.3 | - |
| 2014 | 211,364,001.20 | 198,837,430.84 | 94.1 | - |
| 2015 | 69,771,656.00 | 34,258,564.28 | 49.1 | የመጀመሪያው ሩብ ዓመት |

### ለ) ከካፒታል (የፕሮጀክት ማስፈፀሚያ) በጀት

| ዓ.ም | የተመደበ የፕሮጀክት በጀት | ከተመደበ የፕሮጀክት በጀት የወጣ ወጪ | የወጣ ወጪ በፐርሰንት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 2012 | 380,491,922.94 | 380,491,922.94 | 100 | - |
| 2013 | 298,078,386.48 | 298,078,386.48 | 100 | - |
| 2014 | 378,605,885.72 | 378,605,885.72 | 100 | - |
| 2015 | 122,573,155.70 | 66,060,170.29 | 53.9 | የመጀመሪያው ሩብ ዓመት |

**የኦዲቱ አላማ**

19. የአካባቢ ኦዲቱ አላማ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የፕላስቲክ ምርቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ ያለውን አሰራር ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ፤ እና ውጤታማ እንዲሁም አካባቢ እንዳይጎዳ ታሳቢ ባደረገ መልኩ እየተተገበረ መሆኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ችግሮች ወይም ክፍተቶች ካሉ ችግሮቹን እና መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

**የኦዲት አካባቢ**

20. ለአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ(Audit Area) "የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የፕላስቲክ ምርቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት መገምገም" የሚል ነው፡፡

**የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች**

21. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ሥር ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች የተመረጡ ሲሆን እነሱም፡-

- ባለስልጣኑ በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል ህግና ስርዓት በማዘጋጀት ተግባራዊ ስለማድረጉ መገምገም፤
- የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ ቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነትን መገምገም፤
- ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣አጓጓዝ፣ አወጋገድ በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤ የሚሉ ናቸው፡፡

**የኦዲት መመዘኛ መስፈርት**

22.በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ ሃያ ዘጠኝ (28) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ 513/1999፣ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995፣ የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ክትትልና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጀነራል ተግባርና ኃላፊነት፣ የደረቅ እና አደገኛ ቆሻሻ ህግ ተከባሪነት ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት እና ህግ ተከባሪነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተግባር እና ኃላፊነት ፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995፣ የባለስልጣኑን የ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ እና መልካም ተሞክሮ በማካተት የተዘጋጀ ነው፡፡ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለባለስልጣኑ ተልዕኮ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡባቸው ተደርጓል፡፡ (የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹ **በአባሪ 2** ተያይዘዋል፡፡)

**የአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ**

**የአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ ወሰን**

23.ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ የኦዲት ስታንዳርድ እንዲሁም ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ የአካባቢ ክዋኔ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2011 እስከ 2015 2ኛ ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ያለውን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የፕላስቲክ ምርቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ስርዓት በተመለከተ ያሉትን የሥራ ክንውኖች ነዉ፡፡

**የኦዲቱ ዘዴ**

24.ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት በባለስልጣኑ የተከናወነ ሲሆን በ3 ክልሎች እና 2 ከተማ አስተዳደሮች ስር በሚገኙ 11 የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች፣ 5 የፅዳት አስተዳደር ፅ/ቤቶች፣ 5 የከተማ መዘጋጃ ቤቶች፣ 9 ፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች ፣ 2 ውሃ አምራች ድርጅቶች እንዲሁም 3 ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በአካል በመገኘት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመከለስ፣ የመስክ ምልከታ በማድረግ እና መረጃዎችን በመተንተን ተከናውኗል (ዝርዝሩ **በአባሪ 3** ተያይዘዋል)፡፡

**የደረቅና አደገኛ ቆሻሻ ህግ ተከባሪነትና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት የስራ ሂደት መግለጫ /System Description/**

25. የደረቅና አደገኛ ቆሻሻ ህግ ተከባሪነትና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት የስራ ሂደር ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነቶች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

- የደረቅ የፈሳሽ እና አደገኛ ቆሻሻ አያያዝ ህጎችና ደረጃዎች ተፈጻሚነት የቁጥጥር ዘርፉን ለማሳደግና ለማፋጠን የሚረዳ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል እንዲቀረፅ ድጋፍ ያደርጋል ይቀርፃል ፣ድጋፉ ሲገኝ ተግባራዊ ያደርጋል፣
- የደረቅ የፈሳሽ እና አደገኛ ቆሻሻ አያያዝ ህግ ተከባሪነት ደረጃን የሚገልጽና ለቀጣይ ውሳኔ የሚረዳ የቁጥጥርና ክትትል ሪፖርት መዘጋጀቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ይደግፋል
- የአካባቢ ፖሊሲዎችና ስልቶች ህግጋትና ደረጃዎች በየዘርፉና በየአስተዳደር እርከኑ እንዲተገበሩ የህግ ተከባሪነት ክትትል እና ቁጥጥር ቴክኒካዊ አቅም ግምባታ መርሃ ግብር እንዲኖር ያደርጋል አፈፃጸሙን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤ እና
- የደረቅ ፈሳሽና አደገኛ ቆሻሻ አያያዝ ሥርዓት ተከባሪነት ላይ ያሉ ችግሮች በጥናት መፍትሄ እንዲያገኑ ጥናቶች እንዲካሄዱ ውጤቶችም እንዲተዋወቁ መድረኮችን ያመቻቻል የስራውን አፈጻጸም ይገመግማል የሚሉ ናቸው፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 4 ተያይዘዋል)

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### የደረቅ ቆሻሻ የህግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ስለመደረጋቸው፡

26. ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999 በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ደንቦች እና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ (የህግ ተከባሪነታቸውን ሊያረጋግጥ) እና በጥናት የተለዩ የአካባቢ ችግሮች በስራ ላይ ባሉ ህጎች መቀረፋቸውን በመፈተሽ እና በተለዩ የአካባቢ ችግሮችን ህግ ተከባሪነት ለማስፈፀም የሚያስችሉ አዲስ የህግ ማዕቀፎች እንዲኖር በማድረግ፣ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው እንዲደርስ ሊያደርግ ይገባል፡፡

27.በኦዲቱ ወቅት፡

- በ1989 ዓ.ም የወጣውን የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲን ከቆይታው አንጻር ከነባራዊ ሁኔታ ጋርም ማጣጣም የሚያስፈልግ በመሆኑ ከ2009-2013 ዓ.ም ፖሊሲውንና ለማሻሻል በረቂቅ ደረጃ ዝግጅት በማድረግ በ2013 እና በ2012 ዓ.ም የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999 ለማሻሻል በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ፅ/ቤት መላኩ ተገልጿል፡፡

ይሁን እንጂ፡

- በ1989 ዓ.ም የወጣውን የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲን ለማሻሻል በ2013 ዓ.ም በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ፅ/ቤት የተላከ እና ከተዘጋጀ 2 ዓመት ያስቆጠረ ቢሆንም፤ ፀድቆ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
- በ2012 ዓ.ም የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999 ለማሻሻል በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የተላከው አዋጅ ማሻሻያ እስከ አሁን ፀድቆ ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤
- ነባሩ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999 መሰረት በማድረግ ደንብና መመሪያ ሳይወጣለት ከ15 ዓመት በላይ የቆየ ሲሆን፤ ይህም በመሆኑ በተለያዩ ደረጃዎች በአዋጁ አተገባበር ወጥነትና እርምጃ አወሳሰድ ችግር ማስከተሉ፤
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ 11 የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤቶች፣ 5 ማዘጋጃ ቤቶች እና 5 የፅዳት አስተዳደር ፅ/ቤት በስራ ላይ ያሉ ህጎች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ላይ ያሉትን ችግሮች በመጠኑ መፍታት የሚችሉ ቢሆንም በቂ እንዳልሆኑና የአተገባበር እና የግንዛቤ ችግሮች መኖራቸው፤ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ አዋጅ 513/99 ተከትሎ ዝርዝር ደንብ እና መመሪያ ባለመውጣቱ እርምጃ መውሰድ እንዳልቻሉ የገለፁ መሆኑ፤
- እንዲሁም በየባለስልጣኑ 2012 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም በክልሎች እና ከተማ አስተዳሮች የአካባቢ ጥበቃ ተቋማት የከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ የህግ ተከባሪነት ክትትል ቁጥጥር ተግባራት በ721 ከተሞች ላይ የክትትል እና ቁጥጥር ሥራ እንደተሰራ የሚገልፅ ቢሆንም የኦሮሚያ፣ ድሬዳዋ፣ሶማሊ እና ጋምቤላ ብቻ ማስረጃ የቀረበልን መሆኑ፤
- ባለስልጣኑ በ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ጅማ፣ ጭሮ፣ በደሌ፣ ቦንጋ፣ ሚዛን- ቴፒ፣ ጅግጅጋ፣ ቶጎጫሌ፣ አሳይታ፣ አዋሽ ሰባት፣ ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ደሴ፣ ሀረር እና ድሬደዋ ከተሞች ላይ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህግ ተከባሪነት ክትትልና ቁጥጥር ያደረገ ሲሆን እና ከተሞች የሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ሙሉ ለሙሉ አለመሰብሰብ፣ ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ ጀምሮ ለመቀነስ ስራዎች አለመጀመራቸው፣ ቆሻሻን መለየትና ድጋሚ ጥቅም ላይ እንዲውል አለማድረግ እና የቆሻሻ ቦታዎችን ኦዲት በማድረግ አወጋገዱ ጉዳት እንዳያስከትል በማድረግ ረገድ ጉድለቶች የተለዩ መሆኑ፤

በቃለመጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

28.ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት መልስ፡- በረቂቅ ደረጃ በተዘጋጀው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ

እና የአካባቢ ፖሊሲ የማጽደቅና ተግባር ላይ እንዲውል የማድረግ ሥራ የሚኒስትሮች ምክር ቤትና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመሆኑ መዘግየቱ በዚያ በኩል የተፈጠረ መሆኑን፤ የአካባቢ ፖሊሲን አሻሽሎ ወደ ስርዓት ማስገባትን በተመለከተ ከኦዲቱ መስፈርት እና ወሰን ውጪ መሆኑን እና መረጃ እንዲያቀርቡም ያልተጠየቁ መሆኑን ፤ በተጨማሪም በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999 እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር ስለ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ግዴታዎችን ባለመወጣት ጥፋት በሚፈፅም ሰው ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ የገንዘብ ቅጣቶች መወሰን እና ማስፈፀም እንደሚችሉ የደነገገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

29. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ፡

- በ2012 ዓ.ም ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የተላከው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ባለስልጣኑ ክትትል አድርጎ ለማፀደቅ ግፊት ያደረገበት ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ለኦዲት ያልቀረበ ቡድኑ በመሆኑ እንዲሁም በስራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 513/1999 ደንብና መመሪያ ያልወጣለትና ለስራ አፈፃፀም ትግበራ ምቹ ያልተደረገ በመሆኑ ፤
- የአካባቢ ፖሊሲን ለማሻሻል የተዘጋጀው ረቂቅ ፀድቆ ተግባራዊ እንዲሆን ባለስልጣኑ ክትትል ያደረገበትን ማስረጃ በተደጋጋሚ ጠይቀን ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ እና የአካባቢ ፖሊሲው እስካሁን ፀድቆ ስራ ላይ ያልዋለ በመሆኑ የኦዲት ወሰኑን በሚገባ የሚያካትት በመሆኑ እንዲሁም የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ ውስጥ ባለስልጣኑ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል ህግና ስርዓት በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም የሚል የመጀመሪያ የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ የተቀመጠ በመሆኑ፤
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው ክልሎች/ከተሞች እና ባለድርሻ አካላት ከሃረሪ ክልል የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ 513/1999 አዋጅን ተከትሎ የወጣ ደንብ ቢኖራቸውም በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህግን በተላለፉት ላይ ቅጣትን ለመወሰን የሚያስችል ሃሳብ ያላካተተ በመሆኑ እንዲሁም ሌሎቹ በናሙና የታዩ ባለድርሻዎች አዋጁን ተከትለው ደንብና መመሪያም ሆነ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ ህግ በተላለፉ አካላት ላይ ቅጣት ለመወሰን የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ እንዳላዘጋጁ እና ከባለስልጣኑ የህግ ማዕቀፍ እንዲወጣ ግፊት በማድረግ ጭምር እየተጠባበቁ መሆኑን የተረዳን በመሆኑ እና ባለስልጣኑ የህግ ማዕቀፎችን አዘጋጅቶ ለክልል አካባቢ ጥበቃዎች እና ለከተማ አስተዳድሮች መነሻ የሚሆኑ መመሪያዎችን ያላወጣ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

30. በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጁትን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህጎች ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ክትትል አለማድረግ በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ረቂቆቹ ፀድቀው በስራ ላይ እንዳይውሉ ለማድረጉ እንደ ምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

31. የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅን በማሻሻል ተግባር ላይ ባለመዋሉ እንዲሁም ያለውን አዋጅ መሰረት በማድረግ ደንብና መመሪያ ባለመውጣቱ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዙሪያ የሚታዩ የህግ መተላለፎችን እርምጃ መውሰድ እንዳይቻል ከማድረጉም

በተጨማሪ ከቆሻሻ ሊከተል የሚችልን አሉታዊ ተፅዕኖ እየተከላከሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳውን ማጎልበት የሚያስችል አቅምን በመገንባት ዜጎች በህገ መንግስቱ ያገኙትን በንፁህና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብት እንዳይረጋገጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህጎችና ደረጃዎች ተፈጻሚነት በተመለከተ፡

32. ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ሥርዓት ተከባሪነት ላይ ያሉ ችግሮች በተመለከተ ጥናቶች እንዲካሄዱ ውጤቶችም እንዲተዋወቁ መድረኮችን ሊያመቻችና አፈጻጸሙን ሊገመግም እንዲሁም የህጎቹን ተፈጻሚነት የቁጥጥር ዘርፉን ለማሳደግና ለማፋጠን የሚረዳ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል እንዲቀረፅ ድጋፍ ሊያደርግና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

33. በኦዲቱ ወቅት፡

- <u>የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ሥርዓት ተከባሪነት ላይ ያሉ ችግሮች ለመለየት የሚያስችሉ ጥናቶች ስለማካሄዱ፡</u>
  - ባለስልጣኑ ከዓለም ባንክ ጋር በመሆን እንዲሁም ሲኦል ዩንቨርስቲ (ኮሪያ) የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደርን በተመለከተ ጥናቶች የተጠኑ ሲሆን በጥናቶቹም፡
  - በዓለም ባንክ ጥናት እ.ኤ.አ በ2022 ሶስት ከተሞች አዲስ አበባ፣ ባህርዳር እና ሀዋሳ እንደ ናሙና በመውሰድ በኢትዮጵያ የሚመነጨው ቆሻሻ መጠን እ.ኤ.አ በ2030 10 ሚሊዮን ቶን እንዲሁም እ.ኤ.አ በ2050 18 ሚሊዮን ቶን ሊደርስ እንደሚችል የተገመተ መሆኑ፡
  - የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ሥርዓት ተከባሪ እንዳይሆን እንደ ምክንያትነት ያሉ ችግሮች ያስቀመጠ ሲሆን፤ ለአብነትም፡
    - በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ስርዓት ተከባሪነት ላይ ያሉ ስትራቴጂዎችን ለመተግበር በየከተሞቹ ያሉ የመዘጋጃ ቤት አስተዳደሮች እና ባለሙያዎች በቋሚነትና በቁርጠኝነት ያለመስራት፤
    - በደረቅ ቆሻሻ ዙሪያ የህብረተሰቡ ግንዛቤ አናሳ መሆን እንዲሁም የግል ዘርፉን ተሳትፎ አለማሳደግ፤
    - የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ስርዓት ላይ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎች አለመኖር እንዲሁም በስራ ላይ ያሉ ህጎችን ለማስፈፀም፣ለመቆጣጠር እና እርምጃ ከመውሰድ አንፃር የፈፃሚው አቅም ክፍተት መኖር፤
    - በአገር አቀፍ ደረጃ ደረጃውን የጠበቀ የደረቅ ቆሻሻ የመረጃ አሰባሰብ ስርዓት ባለመኖሩ በከተሞች ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደርን በተመለከተ ውሳኔዎችን ወስኖ ለመስራት እንዳይቻል ያደረገ መሆኑ፤

- ይሁን እንጂ ባለስልጣኑ በጥናቱ ለተጠቀሱ ችግሮች መፍትሄ የሚሆኑ ነጥቦችን በመለየት ወደ ሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማውረድ እንዲተዋወቁ እና እንዲተገበሩ መድረኮችን ያላመቻቸ እና አፈፃፀሙን ያልተከታተለ መሆኑ፤

➢ በኦዲት ቡድኑ በናሙና በታዩ፡

  - የሲዳማ ብ/ክ/መንግስት የአካባቢ የደንና የአየር ለውጥ ባለስልጣን፣ አዳማ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ አዳማ ማዘጋጃ ቤት በደረቅ ቆሻሻ ዙሪያ ጥናት ያደረጉ መሆኑ የገለፁ ቢሆንም ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑ፤
  - የድሬዳዋ የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ባስልጣን፣ የድሬዳዋ ከተማ ፅዳትና ውበት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ የሐረሪ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ የሃረሪ ማዘጋጃ ቤት፣ የሻሸመኔ አካባቢ ጥበቃ እና ከተማ አስተዳደር በደረቅ ቆሻሻ ዙሪያ በክልላቸው/ ከተማቸው የተጠና ጥናት የሌለ መሆኑን፤
  - የጭሮ ከተማ አስተዳደር ሰኔ 2014 ዓ.ም ደረቅ ቆሻሻ በተመለከተ ጥናት ያጠኑ ቢሆንም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን፤

➢ የባለስልጣኑ የደረቅና አደገኛ ቆሻሻ የህግ ተከባሪነት ዳይሬክቶሬት በ2013 ዓ.ም ባደረገው የመስክ ምልከታ ሪፖርት በባህር ዳር፣ በደሴ፣ በጎንደር፣ በቴፒ እና በቦንጋ ከተሞች የሚመነጨው ቆሻሻ መጠንም ይሁን አይነት እንደማይታወቅ እና ይህንን በተመለከተ የተጠና ጥናት የሌለ መሆኑ፤

- <u>የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ የህጎች ተፈጻሚነት የቁጥጥር ዘርፉን ለማሳደግና ለማፋጠን የሚረዳ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል እንዲቀረፅ ስለመደረጉ፡</u>
  ➢ ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህጎችና ደረጃዎች ተፈጻሚነት የቁጥጥር ዘርፉን ለማሳደግና ለማፋጠን የሚረዳ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል መቅረፅን በተመለከተ በዕቅዱ ውስጥ አካቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
  ➢ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ ክልሎች፣ የክልል ከተሞች እና የከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህጎችና ደረጃዎች ተፈጻሚነት የቁጥጥር ዘርፉን ለማሳደግና ለማፋጠን የሚረዳ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ያልቀረፁ መሆኑ እና በባለስልጣኑ የተደረገ ድጋፍ አለመኖሩን የገለፁ መሆኑ፤

በቃለመጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

34. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

  - የህግ ተከባሪነት ላይ ያሉ ክፍተቶች ላይ እ.ኤ.አ በ2015 በወተር ኤይድ የደረቅ ቆሻሻ ማመንጨት ያለበት ደረጃ እና የቆሻሻው ባህሪ በተመለከተ በ20 የኢትዮጵያ ከተሞች የሚያመነጩትን የደረቅ ቆሻሻ መጠን ጥናት የተደረገ መሆኑ እና ጥናቱ ተደራሽ እንዲሆንም የተሰራ መሆኑን እንዲሁም በተለያዩ ዩንቨርስቲዎች የተጠኑ ጥናቶች መኖራቸው፤
  - ደረቅ ቆሻሻ ራሱን ችሎ ፕሮፖዛል ለመቅረፅ የሚደግፉ የዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች የሌሉ መሆናቸው ነገር ግን ከሌሎች አለም አቀፍ ስምምነት ጋር አያይዘው ፕሮፖዛል የሚያዘጋጁ መሆኑን ገልፀው ማስረጃ እንደሚያቀርቡ፤ ከተሞችን የጽዳት ሁኔታ በአብዛኛው የከተማ ልማት

ፈንድ በከተሞች ያለና በከተማ ልማትና መሰረተ-ልማት ሚኒስቴር በኩል መስሪያ ቤቱ አፈጻጸሙን ክትትል የሚያደርግ መሆኑና ከተሞችን በዘላቂነት ለመደገፍ የሚያግዝ ድጋፍ መኖሩ ከግምት ውስጥ ቢገባና ቢታይ የተሻለ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

35. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ ከሌሎች አለም አቀፍ ስምምነት ጋር አያይዘው ፕሮፖዛል የሚያዘጋጁ ስለመሆኑ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ እና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ እራሱን የቻለ ፕሮፖዛሎችን በማዘጋጀት የፋይናንስ ምንጮችን የማፈላለግ ስራዎች ያልተሰሩ በመሆኑ፤ የህግ ተከባሪነት ላይ ያሉ ክፍተቶች ላይ እ.ኤ.አ በ2015 በወተር ኤይድ የደረቅ ቆሻሻ ማመንጨት ያለበት ደረጃ እና የቆሻሻው ባህሪ በተመለከተ የተጠና ቢሆንም ጥናቱ ወደ የሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ ተግባራዊ ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ እንዲሁም ጥናቱ ከተጠና 8 ዓመት የሆነው በመሆኑ በሀገራችን አሁን ያለው የከተሞች መስፋፋትና የህዝብ ቁጥር መጨመር በሀገሪቱ የሚመነጨውን አሁናዊ የደረቅ ቆሻሻ መጠን ለማወቅ የማያስችል በመሆኑ፤እንዲሁም በተለያዩ ዩንቨርሲቲዎች የቀረቡ ጥናቶች ማስረጃ ባለመቅረቡ በኃላፊዎቹ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

36. ባለስልጣኑ ደረቅ ቆሻሻ ራሱን ችሎ ፕሮፖዛል ለመቅረፅ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትር ኃላፊነት ብቻ አድርጎ መወሰድ እና ስራን በባለቤትነት አለመውሰድ እና በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዙሪያ የፈንድ አድራጊ አማራጮችን አለመፈለግ በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህጎችና ደረጃዎች ተፈጻሚነት የቁጥጥር ዘርፉን ለማሳደግና ለማፋጠን የሚረዳ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል እንዳይቀረፅ ለማድረጉ እንደ ምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

37. ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህጎችና ደረጃዎች ተፈጻሚነት ላይ ያሉ የህግ ተከባሪ አለመሆን የተዘረዘሩ ችግሮችን የመፍትሄ ነጥቦች በመለየት ወደ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ባለማውረዱ እንዲሁም የቁጥጥር ዘርፉን ለማሳደግና ለማፋጠን የሚረዳ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል እንዲቀረፅ ባለማድረጉ ችግሮችን ከመነሻቸው ለማስቀረት እንዳይቻል እና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህጎችና ደረጃዎች ተፈጻሚነት እንዳይረጋገጥ አድርጓል፡፡

**የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ፈቃድን በተመለከተ፡**

38. ባለስልጣኑ ማንኛውም ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል የልማት ፕሮጀክቶች ባለቤት ወደ ትግበራ ከመግባቱ በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ በማካሄድ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ፈቃድ ማግኘቱን እንዲሁም በሚመለከታቸው የዘርፍ መ/ቤቶች የተሰጡ የአካባቢና የማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ የይሁንታ ፈቃዶች በህጉ መሠረት እየተገበሩ መሆናቸውን ሊያረጋገጥ ይገባል፡፡

39. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- <u>የልማት ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ በማካሄድ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ፈቃድ ማግኘታቸውን በተመለከተ፡</u>

- ባለስልጣኑ ማንኛውም በአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችሉ የልማት ፕሮጀክቶች ፈቃድ አሰጣጥ ቅድመ ሁኔታዎች ጋር በተያየዘ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ያልተዘረጋና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ተፈፃሚ የሚሆኑባቸውን ፕሮጀክቶች ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1/2001 ውስጥ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚካሄድባቸው የፕሮጀክት ተብለው ከተቀመጡት አንዱ መሰረታዊ ኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ማምረቻ ፋብሪካ የሚል ቢሆንም፣ የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች ኬሚካል በመጠቀም ፕላስቲክ የሚያመርቱ እንደመሆናቸው የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ የሚያቀርቡበት ወጥ የሆነ አሰራር አለመኖሩ፣
- ለክልል ንግድና ኢንዳስትሪ ቢሮዎች በተላለፈ ደብዳቤ መሰረት የቅድመ ንግድ ብቃት ማረጋገጫ (የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማን ጨምሮ) የሚያስፈልጋቸው 10 ዘርፎች ብቻ መሆናቸውን ሆኖም ከነዚህ ውስጥ የፕላስቲክ ምርቶች ያልተካተቱ መሆኑን ይህም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እና የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በመስማማት ወደ ንግድ ቢሮው እንደወረደ የአዲስ አባባ ከተማ አሰተዳደር ንግድ ቢሮ የገለፁ መሆኑ፣
- ከልማት ባንክ ውጪ ፕላስቲክ አምራች ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ አካል አለመኖሩ፣
- የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአገሪቱ ያሉትን የፕላስቲክ ፋብሪካዎችን ዝርዝር በቁጥር የማያውቅ መሆኑ፣
- የኦሮሚያ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፕላስቲክ አምራቾችን በተመለከተ የይሁንታ ፍቃድ አግኝተዉ ወደ ስራ የሚገቡ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም ማስረጃ ያላቀረቡ እና በናሙና ካየናቸው ፕላስቲክ ፋብሪካዎችም የይሁንታ ፍቃዱን ስለማግኘታቸው የማያሳዩ መሆኑ፣ በተጨማሪም የቆሻሻ ማስወገጃ ተቋማት ፈቃድ ለመስጠት መመሪያ የሌለ መሆኑ፣
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን የፕለስቲክ አምራች አልፎ አልፎ ክትትል እንደሚያደረጉ እና ከእነሱ እውቅና ውጪ በድብቅ ፕላስቲክ ምርት የሚመርቱ የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች መኖራቸውን ፣ክትትል በሚያደርጉበት ጊዜ የንግድ ፈቃድም ሆነ የይሁንታ ፍቃድ የሌላቸው ፕላስቲክ አምራች የሚያገኙ መሆኑ፣
- በአዲስ ከተማ እና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በክፍለ ከተማቸው ያሉትን የፕላቲክ አምራች ድርጅቶች አጠቃለው እንደማያውቋቸው በወረዳ ደረጃ የአካባቢ ፅ/ቤት ባለመኖሩ የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች ክትትል ተደራሽ አለመሆኑን እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን ፍቃድ የሚሰጥዋቸው ፕላስቲክ አምራቾች ለክፍለ ከተማቸው የማያሳውቋቸው እና ከከተማ መስተዳደራቸው ጋር የተናበበ ስራ የማይሰሩ መሆኑ፣

- የሐረሪ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እንደገለፀው የቆሻሻ ማስወገጃ ተቋሙ (land fill) የተሟላ የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ በሐረሪ ማዘጋጃ ቤት ያልቀረበበት መሆኑ፤
- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን በ2014 ዓ.ም ማጠቃለያ ሪፖርት ይሁንታ ፈቃድ ሳይዙ ወደ ትግበራ በገቡ 1,200 ነባር ፕሮጀክቶች ላይ ምርመራ በማድረግ የአካባቢና ማህበረሰብ አያያዝ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ለማድረግ ታቅዶ 116 ፕሮጀክቶች (10%) ዕቅዳቸውን ያዘጋጁ ቢሆንም ቀሪው 1184(90%)ዕቅዱን ያላዘጋጁ መሆኑ፤
- በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግስት ደን፣ አካባቢ ጥበቃና ልማት ቢሮ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ የይሁንታ ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓትን በተመለከተ ወጥ የሆነ የአፈጻጸም መመሪያ አለመከተል ክፍተት መኖሩን በ2014 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም ላይ የተገለፀ መሆኑ ፤
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩ 9 ፕላስቲክ አምራች ኢንዱስትሪዎች እና 2 የውሃ አምራች ድርጅቶች፡
  - ✓ 6 የፕላስቲክ አምራች ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ያስጠኑ እና ለሚመለከታቸው አካላት ያቀረቡ መሆናቸው የገለፁ ቢሆንም ማስረጃ ያላቀረቡ፤
  - ✓ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ 2ቱ(ሳራ ፍትዊ ፕላስቲክ ማምረቻ እና ሚኪያስ ፕላስቲክ ማምረቻ) የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲያቀርቡ እንዳልተጠየቁ እና የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ማቅረብ እንዳለባቸው ግንዛቤው እንደሌላቸው የገለፁ እና ግምገማ ያላቀረቡ መሆኑ፤
  - ✓ በኦሮሚያ ክልል የሚገኘው ሙሉጌታ መኮንን ፕላስቲክ አምራች ፋብሪካ የአካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ይሁንታ ፈቃድ ሳያገኝ ስራ የጀመረ እና ኦዲት ሳይደረግ የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ ብቻ እንዲያቀርብ የተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው የታዩ 2 የሃይላንድ ውሃ የሚያመርቱ ድርጅቶች(የአኳ አዲስ እና የስ ውሃ ፋብሪካዎች) የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የይሁንታ ፍቃድ ያገኙ ቢሆንም፤ የሚያመርቱት ምርት ወደ ተጠቃሚ ከደረሰ በኋላ እና ከተጠቀሙት በኋላ ያለው የውሃ ፕላስቲክ ጠርሙስን የአካባቢ ብክለት ሊከላከል/ሊቀንስ የሚያስችል አሰራር በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ውስጥ ያላካተቱ መሆኑ፤

- የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ ደንብ ቁጥር 159/2001 ዓ.ም ተከትሎ በወጣው መመሪያ መሰረት ከ2001 ዓ.ም በኋላ ኬሚካል እና የኬሚካል ውጤቶች ጨምሮ በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚካተት ማንኛውም ነባር ፋብሪካ በአምስት ዓመት ውስጥ የአካባቢ ኦዲት በማካሄድና የአካባቢ አያያዝ ዕቀድ አዘጋጅቶ መተግበር እንዳለበት የሚገልፅ ቢሆንም ባለስልጣኑ በ2013 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች ክትትል ባደረገበት ወቅት ፡
  - በ2001 ዓ.ም በኃላ የተቋቋሙት የፕላስቲክ ፋብሪካዎች ጀማል አወል፣ ሽኳለ ሊን ፣ አህመድ ሙስጠፋ፣ እጥፍወርቅ ፣ አፋር ፉትዊር ፣ ኤርፌሊ፣ የአልኬሲብ፣ ጋዜል፣ ለሰሀ፣ አርጋው፣ ኤርሚያስ፣ ኢትዮ፣ እየሩሳሌም ጌቱ፣

መሀመድ፣ ጥላሁን ባሰው፣ ኤደን ሙሉጌታ፣ ቴዎድሮስ፣ ማይኢረሉ፣ ዛህለፍ፣ ኢኮ፣ ቤኪሞስ፣ አብድራማን፣ ዩዚን እና ነጋ ወልዴ የፕላስቲክ ማምረቻ ፋብሪካዎች ላይ ክትትል ያደረገ ቢሆንም የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ስለማቅረባቸው ክትትል አድርጎ የማያውቅ መሆኑ፤

- ከ2001 ዓ.ም በፊት የተቋቋሙ ነባር የፕላስቲክ ፋብሪካዎች ሴፋ፣ ሪም ኢንዳስትሪያል ፕላስቲክ ማምረቻ እና አያልነህ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ፣ የናና ፕላስቲክ ማምረቻ ደንቡ የአካባቢ ኦዲት ማካሄድና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ አዘጋጅቶ መተግበር እንዳለበት የሚገልፅ ቢሆንም ባለስልጣኑ በዚሁ መልኩ መተግበራቸውን ክትትል ያላደረገ መሆኑ፤

➢ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1994 አንቀፅ 18 እንዳስቀመጠው ማንኛውም የፕሮጀክት ባለቤት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲካሄድበት የተደነገገበትን ማንኛውም ፕሮጀክት ከባለስልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መስሪያ ቤት የይሁንታ ፍቃድ ሳያገኝ ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ጥፋት ፈፅሟልና ከ50 ሺ ብር በማያንስና ከ1 መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል የሚል ቢሆንም ከላይ በኦዲቱ በታዩ የተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ያላጠኑ እና የይሁንታ ፍቃድ ያላገኙ የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች ላይ የተወሰዱ ምንም አይነት እርምጃዎች አለመኖራቸው፡፡

## <u>በውክልና የተሰጡ የይሁንታ ፈቃዶች በህጉ መሠረት እየተገበሩ መሆናቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ፡</u>

➢ ባለስልጣኑ በውክልና የተሰጡ የአካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ የይሁንታ ፍቃዶች ስለመተግበራቸው በተመለከተ ፍቃድ በሰጧቸው አካላት ላይ የይሁንታ ፍቃዶቹን መሰረት በማድረግ ክትትል ስለመደረጉ የማያረጋግጥ መሆኑ፤ ለምሳሌ፡-

- የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በ2005 ዓ.ም ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኢንዱስትሪ ዘርፎች ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች መሰረታዊ የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ማምረቻ ፋብሪካን ጨምሮ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ሰነዶችን የማረጋገጥ ኃላፊነትን የተሰጣቸው ቢሆንም ባለስልጣኑ ክትትል ያደረገበት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ
- የክልል እና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የሰጧቸውን የይሁንታ ፍቃዶች በፍቃዶቹ መሰረት ክትትል ስለማድረጋቸው ባለስልጣኑ የማያረጋግጥ መሆኑ፤

➢ ባለስልጣኑ በክልል እና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች ላይ የአካባቢና የማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ በህጉ መሠረት እየተገበሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ክትትል አድርጎ የማያውቅ መሆኑ፤

➢ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ባለስልጣን የ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ በማካሄድ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ ትግበራ የገቡ ፕሮጀክቶችን በወጡ

የአሰራር መመሪያዎች መሰረት መተግበራቸውን እና በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ አለማድረሳቸውን ክትትል ለማድረግ ታቅዶ 39% ብቻ የተከናወነ መሆኑ፤

- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን በ2014 ዓ.ም ማጠቃለያ ሪፖርት ይሁንታ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ ስራ የገቡ 5,500 ፕሮጀክቶች በገቡት ውለታ መሰረት መተግበራቸውን በክትትል ለማረጋገጥ ታቅዶ 2,168(39.4% ) ብቻ ክትትል የተደረገ መሆኑ፤

በቃለመጠይቅ፣ በመስክ ምልከታ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

40. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡- የቅድመ ንግድ ብቃት ማረጋገጫን በተመለከተ በባለስልጣኑ ስምምነት የፕላስቲክ ማምረቻዎችን ሳያካትት ለክልሎች ተላልፏል ስለተባለው ኦዲት ግኝት ከባለስልጣኑ ጋር የተደረገ ስምምነትም አለመኖሩን፤ ከሁለት አመት በፊት የአካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ የይሁንታ ፈቃድ እንዲሰጡ እና ክትትል እንዲያደርጉ ለተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ውክልና ተሰጥቷቸው እንደነበረ በዚህ ወቅትም በሴክተራቸው ስር ለሚገኙ በክልል ላሉ መ/ቤቶች እንዲተገብሩ ወደ ታች ያላወረዱ በመሆኑ የአፈፃፀም ክፍተቶች የታዩ መሆኑን ሆኖም በአሁኑ ወቅት መሠረታዊ ኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶችን ማምረት የፕላስቲክ አምራቾችን ጨምሮ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ እንዲያቀርቡ በማድረግ በብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት እንዲያልፍ እየተደረገ መሆኑን ነገር ግን በዘርፉ የተሠማሩ ድርጅቶች የይሁንታ ፍቃድ ሳያገኙ ሥራ ላይ ተሠማርተው የሚገኙ እንደሚያጋጥሙ እና እነዚህን ድርጅቶች የአካባቢ ኦዲት በማካሄድ የአካባቢና የማህበረሰብ አያያዝ ዕቅድ እንዲያዘጋጁና በሚመለከታቸው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት እንዲያፀድቁና ሥራቸውን እንዲቀጥሉ የማድረግ ሥራ በትኩረት እየተሠራ ያለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

41. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ ባለስልጣን መ/ቤቱ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ በተመለከተ ኃላፊነት የተሰጠው ቢሆንም ከሚመለከታቸው አካላት ንግድ ሚኒስቴርን ጨምሮ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማን በተመለከተ የዘረጋው ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት የሌለ በመሆኑ የፕላስቲክ አምራቾች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ እንዲያቀርቡ በማድረግ እየተሰራ ስለመሆኑ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ በተጨማሪም የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ ደንብ ቁጥር 159/2001 በተቀመጠው መሰረት ከ2011 ዓ.ም በፊት የተቋቋሙ ነባር የፕላስቲክ አምራች ድርጅት በናሙና ከታዩት እና በባለስልጣኑ በ2013 ዓ.ም ክትትል በተደረገባቸው 4 ነባር እና 32 አዲስ የፕላስቲክ ፋብሪካዎች በደንቡ መሰረት እንዲተገበሩ ያልተደረጉ በመሆናቸው መልሱን አልተቀበልነውም፡፡

42. ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ በመሆኑ፣ የፕላስቲክ ምርቶች የሚያስከትሉትን ብክለት አሳንሶ የማየት እና የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች ክትትል ለማረግ በተከታታይ ዓመታት በዕቅድ ያለመያዝ ችግር በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ተፅእኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ የልማት ፕሮጀክቶች(የፕላስቲክ ፋብሪካዎች እና

የቆሻሻ ማከማቻ ላንድ ፊል) የተፅዕኖ ግምገማ በትክክል አሰርተው ተግባራዊ እንዳያደርጉ እንደ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

43.ማንኛውም ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል የልማት ፕሮጀክቶች ባለቤት ወደ ትግበራ ከመግባቱ በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ የይሁንታ ፈቃድ በማግኘት ወደ ስራ እንዲገቡ እና በፍቃዱ መሰረት ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ክትትል ባለመደረጉ ህገ ወጥ የፕላስቲክ ምርቶች እንዲበራከቱ እና አካባቢን እንዲበክሉ ከማረጉም በተጨማሪ በሰው እና በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡

## የፕላስቲክ አምራች ተቋማት ክትትል በተመለከተ፡

44.ባለስልጣኑ ውፍረታቸው 0.03 ሚ.ሊ ሜትርና ከዚያ በታች ሆነው በስብሰው ከአፈር ጋር የማይዋሃዱ የፕላስቲክ ምርቶችን ተለይቶ ለተገለፀ አገልግሎት በቀር ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም በአገር ውስጥ እንዳይመረቱ ሊያደርግ እንዲሁም የተቋማቱን ክትትል ዘገባ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

45.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ 18 የፕላስቲክ ከረጢትና መጠቅለያ አምራች ድርጅቶች ላይ የተደረገ የህግ ተከባሪነት ክትትል ከ18 የፕላስቲክ አምራች ተቋማት 65 ናሙናዎች ላይ ልኬት የተደረገባቸው ሲሆን 45 ናሙናዎች በህግ ከተፈቀደው 0.03 ሚ.ሊ ሜትር እና ከዛ በታች ሲሆኑ 18 አምራች ተቋማት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ህገ ወጥ የፕላስቲክ ከረጢት እና መጠቅለያ እያመረቱ መሆኑ፤
- በባለስልጣኑ በ2013 ዓ.ም በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች ክትትል ባደረገበት ወቅት በሰበታ ክትትል ካደረገባቸው 11 የፕላስቲክ አምራች ፋብሪካዎች 10 የፕላስቲክ አምራች ፋብሪካ እና በቡራዮ 17 ፕላስቲክ አምራች ፋብሪካ በተደረገ ክትትል ደግሞ 13 የፕላስቲክ አምራች አዋጁ ላይ በተቀመጠ ህግ መሰረት የማይሰሩ መሆናቸውን ያረጋገጠ ቢሆንም ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያላደረገ መሆኑ፤
  - በተጨማሪ በ2010 ዓ.ም ፣ በ2011 ዓ.ም እና በ2013 ዓ.ም የኦሮሚያ ክልል ከተሞች የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች የህግ ተከባሪነት ክትትል ባደረገበት ወቅት በሰበታ ጀማል አወል የፕላስቲክ ድርጅት እና በቡራዩ አብደራህማን የፕላስቲክ ፋብሪካ በ3ቱም ዓመታት በተደጋጋሚ በህግ ከተፈቀደው 0.03 እና ካዛ በታች እያመረቱ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ የሌለ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአዲስ ከተማ እና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞች የፕላቲክ አምራች ድርጅቶች በአዋጅ በተቀመጠው ህግ ስለመስራታቸው የሚለኩበት ማክሮ ሜትር(Micrometer) የሌላቸው እና ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትል ለማድረግ እንዳይችሉ ያደረገ መሆኑ፤

- የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በከተማ አስተዳደሩ ስር የሚገኙ አዲስ ከተማ እና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞች፣ የኦሮሚያ ክልል እና በክልሉ ስር የሚገኙ አዳማ፣ ሻሸመኔ፣ም/ሐ/ዞን እና ሞጆ ከተሞች፣ የሃረሪ ክልል፣ የሲዳማ ክልል የሚገኙ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች የሚያመርቱት የፕላስቲክ ከረጢት በህጉ በተቀመጠው ውፍረት ልክ መሰረት እያመረቱ መሆን አለመሆኑን ለክተው የሚያረጋግጡበት ማክሮ ሜትር (Micrometer) መሳሪያ የሌላቸው መሆኑን ይህም ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትል ለማድረግ እንዳይችሉ ያደረገ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ከተማ ክ/ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ፅ/ቤት (መርካቶ) ለ1 ፕላስቲክ አምራች ድርጅት ብቻ ፈቃድ የተሰጠ ቢሆንም በክፍለ ከተማው ባሉ ወረዳዎች (1፣2፣3፣6፣7 እና 8) ብዙ ተደብቀው ስስ ፌስታል የሚያመርቱ መኖራቸው፤ ገበያውም በስስ ፌስታል የተጥለቀለቀ መሆኑን እንዲሁም የስራ ፈቃድ ከሚሰጡ ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የመስራት ችግር መኖሩ፤
- በሐረሪ፣ በምዕ/ሐ/ዞን በጭሮ፣ ሞጆ ከተሞች ምንም አይነት ፕላስቲክ የሚያመርቱ ድርጅት የሌሉ ቢሆንም ከተሞቹ ላይ ከሌሎች ከተሞች የሚገቡ በርካታ ፕላስቲክ ምርቶች በገበያ መኖራቸው እና ወደ ከተሞቹ የሚገቡት የፕላስቲክ ምርቶች ላይ በየክልሉ /ከተሞቹ(ከተሞች ማዘጋጃ ቤቶች) ያሉ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በህጉ በተቀመጠው ውፍረት ልክ ስለመሆናቸው የቁጥጥር ስራ ያልተሰራ መሆኑ፤
- በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ 9 የፕላስቲክ አምራች ፋብሪካዎች የፕላስቲክ ውፍረት መለኪያ ያላቸው ዩኒክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና አብድል አዚዝ የፕላስቲክ ውጤቶች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ብቻ መሆናቸው የተቀሩት 7ቱ በህጉ በተቀመጠው ውፍረት ልክ መሰረት እያመረቱ መሆኑ አለመሆኑን የማያረጋግጡ እና ህጉንም የማያውቁት መሆኑ፤ እንዲሁም ዘጠኙ የፕላስቲክ አምራቾች ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማይልኩ መሆኑ፤
- ባለስልጣኑ በ2011 ዓ.ም በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል ከተሞች ማለትም በሰበታ 6፣ በቡራዩ 10፣ በዱከም 5፣ በሱልልታ 2 እና በለገጣፎ 1 በአጠቃላይ 24 የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች ላይ የህግ ተከባሪነት ክትትል ባደረገበት ወቅት ድርጅቶቹ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ህገ ወጥ የፕላስቲክ ከረጢት ወይም መጠቅለያ የሚመርቱ መሆኑን የተረጋገጠ ቢሆንም ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያላደረገ መሆኑ፤
- ባለስልጣኑ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ የተወሰኑ የፕላስቲክ ፋብሪካዎች ላይ በ2013 ዓ.ም የፕላስቲኩ ውፍረት አዋጅ ላይ በተቀመጠው መሰረት መመረቱን ክትትል ያደረጉበት ማስረጃ የቀረበ ቢሆንም በክልሉ ያሉ አብዛኛውን የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች ያልሸፈነ እንዲሁም በሌሎች ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ያሉ የፕላስቲክ ምርት አምራች ድርጅቶች ላይ የሚያመርቱት

የፕላስቲክ ምርት ውፍረት አዋጅ ላይ በተቀመጠው መሰረት መመረቱ ክትትል የማያደርጉ መሆኑ፤

- ባለስልጣኑ በ2012 እና 2014 ዓ.ም የትኛውም የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች እንዲሁም በ2013 ዓ.ም ከላይ ከተጠቀሱት የተወሰኑ የኦሮሚያ ከተሞች ውጪ ክትትል በማድረግ ዘገባ ያላዘጋጁ መሆኑ፤
- የባለስልጣኑ 2012 በጀት ዓመት ዕቅድ በፕላስቲክ አምራች ተቋማት ላይ የክትትልና ቁጥጥር ዘገባ ማዘጋጀት በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ያልተከናወነ መሆኑ፤
- ባለስልጣኑ ተለይተው ከተፈቀዱ ፕላስቲክ ምርቶች ውጪ ወደ አገር ውስጥ አለመግባታቸውን ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትል የማያደርግ መሆኑ፤

በቃለመጠይቅ፣ በመስክ ምልከታ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

46. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡- ባለስልጣኑ ተለይተው ከተፈቀዱ ፕላስቲክ ምርቶች ውጪ ወደ አገር ውስጥ አለመግባታቸውን በተመለከተ ንግድ ሚኒስቴር ፍቃድ ሲሰጥ መቆጣጠር እንዳለበት ሆኖም በባለስልጣኑ የተደረጉ ክትትል ማስረጃዎች እንደሚያቀርብ ገልፀው የፕላስቲክ ከረጢት በገበያ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ያልተሰጠ መሆኑን፣ በገበያ ያለውን የፕላስቲክ ከረጢት ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ በተመለከተ በረቂቅ ደረጃ በሚገኝ አዋጅ የተካተተ መሆኑን፤ ባለስልጣኑ ፕላስቲክ አምራች ድርጅቶችን በየሁለት ዓመቱ ልዩነት 2011ዓ.ም፣ 2013ዓ.ም እና በ2015 ዓ.ም ክትትልና ቁጥጥር ስራ በዓመታዊ ዕቅድ አካቶ እየሰራ እንደሚገኝ ትኩረታቸው በድሬዳዋ፣ አዲስ አበባ እና በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች መሆኑን ገልፀዋል፡፡
47. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ ተለይተው ከተፈቀዱ ፕላስቲክ ምርቶች ውጪ ወደ አገር ውስጥ አለመግባታቸውን በተመለከተ በ2014 ዓ.ም ለ2 ድርጅት ብቻ ከ0.03 ሚ.ሜትር በላይ መሆናቸውን እና የፕላስቲክ ከረጢቱ እንዲለቀቅላቸው ባለስልጣኑ ያስመለከተ ሲሆን በ2013 ዓ.ም 2 ድርጅቶች፣ በ2014 ዓ.ም 4 ድርጅቶች እና በ2015 ዓ.ም 3 ድርጅቶች ከጉምሩክ ፅ/ቤት የፕላስቲክ ከረጢቱ አካባቢያዊ ተቀባይነት ያለው መሆኑ ማስረጃ እንዲያቀርቡ በተጠየቁት መሰረት ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በደብዳቤ የጠየቁ ቢሆንም ባለስልጣኑ ክትትል በማድረግ የሰጣቸው መልስ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፤ የፕላስቲክ ከረጢት በተመለከተ ማንኛውም የአካባቢ ብክለት የሚያስከትል ነገር የመቆጣጠር ሃላፊነት የባለስልጣኑ በመሆኑ እንዲሁም ከሁለቱ ከተማ መስተዳደሮች እና ከኦሮሚያ ክልል ውጪ የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች አለመኖራቸውን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያላረጋገጡ በመሆኑ ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡
48. ባለስልጣኑ ፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች ክትትል በዓመታዊ እቅዱ ላይ አካቶ የማይሰራ በመሆኑ በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ፕላስቲክ አምራች ድርጅቶችን አዋጁ ላይ በተቀመጠው ህግ መሰረት ማምረታቸውን ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትል አድርጎ ዘገባ በማዘጋጀት እርምጃ እንዲወሰድባቸው እንዳይቻል ለማድረጉ እንደ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

49. ፕላስቲክ አምራች ድርጅቶችን አዋጁ ላይ በተቀመጠው ህግ መሰረት ማምረታቸውን ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትል ባለማድረጉ ህገ ወጥ የፕላስቲክ ምርቶች ያለአግባብ እንዲመረቱ እና በስፋት እንዲሰራጩ በማድረግ ለአካባቢ ብክለት አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡

**የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ የፕላስቲክ ምርቶችን በሌሎች ተተኪ ምርቶች ስለመለወጥ እና የፕላስቲክ አምራቾች ምርቶቻቸውን ስለመሰብሰብ፡**

50. ባለስልጣኑ የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ የፕላስቲክ ምርቶችን የሚያመርቱ አምራቾች በጊዜ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ምርቱን የሚያቋርጡበትን እና በሌሎች ተተኪ ምርቶች የሚለውጡበትን እንዲሁም ያመረቷቸው ምርቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ የሚሰበስቡበትና መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉበት አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

51. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- በድሬዳዋ፣ በሐረር በምዕ/ሐ/ዞን፣ በሲዳማ ፣ በሻሻመኔ፣ በአዳማ እና በሞጆ የአካባቢ የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ የፕላስቲክ ምርቶችን የሚያመርቱ አምራቾች በጊዜ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ምርቱን የሚያቋርጡበትን እና በሌሎች ተተኪ ምርቶች የሚለውጡበት እንዲሁም የፕላስቲክ አምራች ተቋማት ያመረቷቸው ምርቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ የሚሰበስቡበትና መልሰው ጥቅም ላይ የሚያውሉበት አሰራር ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤

- ባለስልጣኑ የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ ለአንድ ጊዜ አገልግሎት የሚውሉ ማሸጊያዎች (ለምሳሌ፡ የፕላስቲክ ከረጢት/ፌስታል፣ የታሸገ ውሃ፣ የለስላሳ መጠጥ እና የተለያዩ የመጠጥ ምርቶች መያዣዎች) የፕላስቲክ ምርቶችን የሚያመርቱ አምራቾች በጊዜ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ምርቱን የሚያቋርጡበትን በሌሎች ተተኪ ምርቶች የሚለውጡበትን ስርዓት ያልዘረጋና ይልቁንም ቀደም ሲል የሚያመርቱትን ምርት በጠርሙዝ የሚያቀርቡ የነበሩ የለስልሳ መጠጥ ፋብሪካዎች ወደ ፕላስቲክ ውሃ ኮዳ የቀየሩና ባለስልጣኑ ክትትል በማድረግ እርምጃ ያልወሰደባቸው መሆኑ እንዲሁም የፕላስቲክ አምራች ተቋማት ያመረቷቸው ምርቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ የሚሰበስቡበትና መልሰው ጥቅም ላይ የሚያውሉበት አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤

በቃለመጠይቅ፣ በመስክ ምልከታ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

52. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡- የፕላስቲክ ምርቶችን በጊዜ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ምርቱን የሚያቋርጡበትን አሰራር ባሉ የህግ ማዕቀፎች ሥርዓት ዘርግቶ ወደ ስራ ለማውረድ በህግ ያልተካተተ በመሆኑ ለመተግበር አለመቻሉን ይህንንም ችግር ለመቅረፍ በተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ አካተው ያቀረቡ መሆኑን፤ የፕላስቲክ አምራች ተቋማት ያመረትዋቸው ምርቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ የሚሰበስቡበትና

መልሰው ጥቅም ላይ የሚያውሉበት አሰራር ግን በባለስልጣኑ ያልተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

53. በስራ ላይ ያሉ የህግ ማዕቀፎች የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ የፕላስቲክ ምርቶችን በጊዜ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ምርቱን የሚያቋርጡበትን እና በሌሎች ተተኪ ምርቶች የሚለውጡበትን እንዲሁም የፕላስቲክ አምራች ተቋማት ያመረቷቸው ምርቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ የሚሰበስቡበትና መልሰው ጥቅም ላይ የሚያውሉበት አሰራር የማይደግፉ በመሆኑ ለክፍተቶቹ እንደ ምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

54. የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ የፕላስቲክ ምርቶችን የሚያመርቱ አምራቾች በጊዜ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ምርቱን የሚያቋርጡበትን እና በሌሎች ተተኪ ምርቶች የሚለውጡበትን አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ ህገ ወጥ ፕላስቲክ ምርት እንዲጨምር ከማድረጉም በተጨማሪም ቀደም ሲል ጠርሙስ የሚጠቀሙ የለስላሳ መጠጥና የፍራፍሬ ጭማቂ ፋብሪካዎች ወደ ፕላስቲክ ጠርሙስ መጠቀም እንዲገቡ እንዲሁም የፕላስቲክ አምራች ተቋማት ያመረቷቸው ምርቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ የሚሰበስቡበትና መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉበት አሰራር ባለመዘርጋቱ ፕላስቲኮቹ ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ በየአካባቢው ተዝረክርከው እንዲገኙ እና አካባቢን እንዲበክሉ ከማድረጉም በተጨማሪ በሰውና በእንስሳት ጤና ላይ ችግር እንዲፈጥሩ በር ከፍቷል፡፡

**የፕላስቲክ ቆሻሻ የሚያደርሰው ጉዳት ጥናት እና የአካባቢ አያያዝ ግንዛቤ ማስፋፊያን በተመለከተ፥**

55. ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ቆሻሻ በአካባቢ፣ በሰው እና በእንስሳት የሚያደርሰውን ጉዳት በተመለከተ ጥናት በማድረግ በጥናቱ መሰረት ለዘርፍ መ/ቤቶች እና ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥ እንዲሁም የከተማ አስተዳደሮች የአካባቢ ግንዛቤ ማስፋፊያ ተግባራትን ማቀዳቸውን እና መተግበራቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- <u>ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ቆሻሻ በአካባቢ፣ በሰው እና በእንስሳት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ጥናት መደረጉን በተመለከተ፡</u>
  - ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ቆሻሻ በአካባቢ፣ በሰው እና በእንስሳት የሚያደርሰውን ጉዳት በተመለከተ ጥናት ያላደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም የጉዳቱን መጠን ለመረዳት እና የመፍትሄ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል መነሻ ለማግኘት፡
    - የፕላስቲክ ምርት በየዓመቱ በሀገር ውስጥ ምን ያህል እንደሚመረት እና ከውጭ ሀገር ምን ያህል እንደሚገባ፣
    - በአገር ውስጥ ከተመረቱት እና ከውጭ አገር ከገቡ የፕላስቲክ ምርቶች ውስጥ በቆሻሻ መልክ ከሚጣለው የሚሰበሰበው እና መልሶ ጥቅም ላይ የሚውለው ምን ያህል እንደሆነ መረጃ በማሰባሰብ ወይም በጥናት የማይታወቅ መሆኑ፤

- <u>ባለስልጣኑ ስለ ፕላስቲክ ምርቶች ጉዳት ግንዛቤ ስለመስጠቱ እንዲሁም የከተማ አስተዳደሮች የአካባቢ ግንዛቤ ማስፋፋትን በዕቅድ አካተው ስለመተግበራቸው ክትትል ስለመደረጉ በተመለከተ፡</u>
  - የኦሮሚያ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እና በክልሉ የሚገኙ ም/ሐ/ዞን፣ ሻሸመኔ ፣ ሞጆ እና አዳማ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን፣ የድሬዳዋ የአካባቢ ጥበቃ፣ የሲዳማ የአካባቢ ጥበቃ እና ሃረሪ የአካባቢ ጥበቃ የአካባቢ ጥበቃ የአካባቢ ግንዛቤ ማስፋፊያ ተግባራትን በዕቅድ በማካተት እየተሰሩ መሆኑን ሆኖም ተደራሽ አለመሆኑን እና በፕላስቲክ ቆሻሻ አያያዝ ላይ ለውጥ ያላመጣ መሆኑ፤
  - በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የክልል እና ከተማ አስተዳደሮች ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ምርቶች በአካባቢ፣ በሰው እና በእንስሳት የሚያደርሰው ጉዳት በተመለከተ ቋሚ እና ተከታታይ በሆነ መልኩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ያልሰጠ እንዲሁም የከተማ አስተዳደሮች የአካባቢ ግንዛቤ ማስፋፋትን በዕቅድ አካተው ስለመተግበራቸው ክትትል ያላደረገ መሆኑ፤

በቃለመጠይቅ፣ በመስክ ምልከታ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

56. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፡- ከጤና እና ከአካባቢ ብክለት አንፃር ካለው ጉዳት በመነሳት የፕላስቲክ ሃይላንዶች ቀለም ማስቀረት እና የአንገት ሽፋን (Neck Seal) ጥናት ተጠንቶ የተስተካከለ መሆኑ እና በባለስልጣኑ በዓመት 20 ከተሞች ክትትል እንደሚያደርጉ እና ክልል ከሚያደርጉት ክትትል ጋር ሲደመር በዓመት 700 ከተሞች ክትትል እንደሚያደጉ እንዲሁም በትምህርት ቤቶች ላይ እና በኢትየዮጵያ ሬድዮ በሳምንት አንዴ ለ20 ደቂቃ ያህል ግንዛቤ የመፍጠር ስራ እንደሚሰራ ሆኖም በቂ እና ተደራሽ አለመሆኑን እንዲሁም በዘርፍ መ/ቤቶች እና በህብረተሰቡ ላይ የግንዛቤ የአፈጻጸም ክፍተት መኖሩን የተለየ መሆኑ ገልፀዋል፡፡
57. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ የፕላስቲክ ቆሻሻ ጨምሮ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና የሚያሳድረው ተፅዕኖ በተመለከተ በቂ ጥናት በማድረግ ለሚመለከታቸው የአካባቢ አያያዝ ተግባሪ አካላት ግንዛቤ ስለመፈጠሩ የሚያረጋግጥበት አሰራር የሌለው በመሆኑ የአቅም ክፍተት መለየቱን ብቻ እንደ በቂ ስራ አፈፃፀም አልወሰድነውም፡፡
58. የፕላስቲክ ቆሻሻን ጨምሮ የደረቅ ቆሻሻ የሚያደርሱት ጉዳት በአግባቡ ተረድቶ ትኩረት አለመስጠት በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ በጥናት እንዳይለይና በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚመለከታቸው አካባቢ አያያዝ ተግባሪ አካላት እና ህብረተሰቡ ግንዛቤ ተደራሽ በሆነ መልኩ እንዳይፈጠር ስለማድረጉ እንደ ምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡
59. በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ስርዓት በተመለከተ ጥናት ባለመደረጉ በሀገር ደረጃ ከየከተሞች የሚመነጩ ደረቅ ቆሻሻ በዓመት ምንያህል እንደሆነ እንዳይታወቅ፣ በሀገሪቱ ምን ያህል የፕላስቲክ ምርቶች እንደሚመረቱ እና ጥቅም ላይ

እንደሚውሉ እና ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ በአግባቡ ባለመሰብሰባቸው የሚያደርሱት ጉዳት እንዳይታወቅ አድርጓል፡፡ እንዲሁም በሃገር አቀፍ ደረጃ የፕላስቲክ ቆሻሻ ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እየጨመረ እንዲመጣ ፤የፕላስቲክ ቆሻሻ እርሻን ጨምሮ የማህበረሰቡ አኗኗር እና ጤና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲያስከትል፤እንስሳት ላይ የፕላስቲክ ቆሻሻ ከሚመገቡት እና ከሚጠጡት ውሃ ጋር እየተቀላቀለ እስከሞት የደረሰ የጤና ጉዳት ማስከተሉን፤ በተጨማሪ የፕላስቲክ ቆሻሻ በከፍተኛ ሁኔታ የውሃ አካላትን፣አፈርን፣አየርን(ሲቃጠል) በጠቅላላው አካባቢን እንዲበከል ያደረገው ሲሆን ለሚመለከታቸው አካባቢ አያያዝ መ/ቤቶች እና ህብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲፈጠር ባለመደረጉ የአካባቢ አያያዝ ላይ ሁሉም የድርሻውን እንዳይወጣ ያደርገዋል፡፡

## የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ስለመዘጋጀታቸው፡

60. ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ዝቅተኛውን የአስተዳደር እርከናቸውንና የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ ባሳተፈ መልኩ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀታቸውንና ተግባራዊ ማድረጋቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል::
61. ይሁን እንጂ

- የድሬዳዋ፣ ሐረሪ፣ጭሮ፣ሃዋሳ፣ ሻሸመኔ፣ ሞጆ፣ አዳማ ከተሞች(የከተሞች ማዘጋጃ ቤቶች) ዝቅተኛውን የአስተዳደር እርከናቸውንና የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ ባሳተፈ መልኩ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ የማያዘጋጁ መሆኑ፤
- የባህርዳር፣ ደሴ፣ ጎንደር፣ ቴፒ እና ቦንጋ ከተሞች ማዘጋጃዎች የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እቅድ ያላዘጋጁ መሆኑ፤
- ከተማና የመሰረተ ልማት ሚኒስቴር በኢትዮጵያ 2,433 ከተሞች ወደ ደረቅ ቆሻሻ ስርዓት የገቡ መሆናቸውን የገለፁ ቢሆንም በባለስልጣኑ ከተሞቹ መኖራቸውንም ሆነ ወደ ደረቅ ቆሻሻ ስርዓት የገቡ ስለመሆናቸው የማይታወቅ መሆኑ፤
- በኢትዮጵያ 2,433 ከተሞች ወደ ደረቅ ቆሻሻ ስርዓት የገቡ ቢሆኑም በባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ዝቅተኛውን የአስተዳደር እርከናቸውንና የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ ባሳተፈ መልኩ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀታቸውንና ተግባራዊ ማድረጋቸውን ክትትል ስለማድረጉ ሲታይ፡
    - ባለስልጣኑ በ2013 ዓ.ም ዕቅድ ላይ አጠቃላይ 750 ከተሞች ክትትልና ቁጥጥር እንደሚደረግ ያስቀመጠ መሆኑን እና በበጀት ዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም 739 ከተሞች ክትትልና ቁጥጥር እንዳደረገ ያስቀመጠ ቢሆንም ባለስልጣኑ በራሱ ስንት ከተሞች ክትትል እንደሚያደርግ ዕቅድ ያልያዘ መሆኑን እና በክልሎችና በከተማ መስተዳድሮች ከሚገኙ የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤቶች በ2013 ዓ.ም የክትትል ሪፖርት ያልተቀበለ መሆኑ፤
    - በባለስልጣኑ 2014 ዓ.ም ዕቅድ ላይ 50 ከተሞች የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ እና እንዲተገብሩ ድጋፍ ለማድረግ ያቀደ ቢሆንም በበጀት አመቱ 18 (36%) የደረቅ ቆሻሻ ዘገባ (አዳማ፣

ቢሾፍቱ፣ አሰላ፣ ቡሌሆራ፣ ዲላ፣ ይርጋጨፌ፣ አዋሳ፣ ሻሸመኔ፣ ሳውላ፣ አርባምንጭ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ጂንካ፣ ኮንሶ/ካራት፣ ድሬደዋ፣ ሀረር፣ ጭሮ፣ ጅጅጋ እና ገለምሶ) ላይ የተከናወነ ሲሆን ሁሉም ክትትል እና ቁጥጥር የተደረገባቸው ከተሞች የተቀናጀ የደረቅ አያያዝና አወጋገድ እቅድ የሌላቸው መሆኑ፣

- የባለስልጣኑ 2014 ዕቅድ አፈፃፀም በአጠቃላይ በክልልና በከተማ አስተዳደሩ 818 ከተሞች ላይ ክትትል እንደተሰራ የገለፅ ቢሆንም ከክልል የአካባቢ ጥበቃዎች ሪፖርት የላኩ ኦሮሚያ ክልል ፣ የአማራ ክልል፣ ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ ሶማሊ ክልል፣ ደቡብ ብ/ብ/ህ ክልል እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዕቅድ አፈፃፀም ብቻ በማስረጃነት ለኦዲት ቡድኑ ያቀረበ መሆኑ እና
- ከ2012 እስከ 2014 ዓ.ም በባለስልጣኑ በተደረገው ክትትል የሚታዩ ክፍተቶች ግብረመልስ የሚሰጡት ለከተማ አስተዳደሮች ሳይሆን ለክልል የአካባቢ ጥበቃ መሆኑን እና ባለስልጣኑ የሰጠውን ግብረ-መልስ ተግባራዊ መደረጉ የሚከታተልበት አሰራር ስርዓት የሌለው መሆኑ፤

በቃለመጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

62.ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት መልስ፡- ከክልል አካባቢ ጥበቃ እና ከከተሞች በተከታታይ በየሩብ ዓመቱ እና በየዓመቱ ግምገማ የሚያደርጉ መሆናቸው እና በቃል ግብረ መልስ እንደሚሰጡ፤ ክትትል ሲያደርጉ ለከተማ ልማት ሚኒስቴር እና ለክልል አካባቢ ጥበቃ ግብረ መልስ እንደሚልኩ፤ ለክልሎች የሚሰጥ ግብረ መልስ ክልሎች በቅርበት ክትትልና ድጋፍ እንዲያደርጉ ታስቦ መሆኑ እና ክትትልና ቁጥጥር ስራ ከክልሎች ጋር በጋራ እንደሚያደርጉ ሆኖም ግብረ መልሱ ወደ ከተሞች መድረሱ ክትትል የሚያደርጉበት አሰራር የሌለ መሆኑን፤ የተጠያቂነት ስርዓቱ ደካማ በመሆኑ ባለስልጣኑ ክትትል ባደረገባቸው ከተሞች የታዩ ክፍተቶች ላይ እርምጃ እንደማይወሰድ እና የህግ ክፍተት በመኖሩ እርምጃ መውሰድ አለመቻላቸው፤ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዝግጅት እና ትግበራ የከተማ ልማት ሚኒስቴር በሚገልጸው መጠን የሌለ መሆኑን፣ የማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ይህን ያክል ከተሞች ስለመኖራቸው መረጃው የማያመለክት መሆኑን ገልፀው የባለስልጣኑ ክትትልና ድጋፍ መነሻ የባለስልጣኑ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

63.ኃላፊዎቹ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዝግጅት እና ትግበራ የከተማ ልማት ሚኒስቴር በሚገልጸው መጠን የሌለ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ክትትል በሚያደርግበት ወቅት ምንም መነሻ የሌለው በመሆኑ፤ከስታስቲክስ ኤጀንሲ እና ከባለስልጣኑ ወደ ደረቅ ቆሻሻ ስርዓት የገቡ የከተሞች ዝርዝር የሚያሳይ ማስረጃ ቢጠየቅም ያላቀረቡ በመሆኑ፤ ባለስልጣኑ በ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ላይ 1960 ከተሞች የተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝ ስርዓት መዘርጋቱን ክትትልና ቁጥጥር እንደሚያደርግ ያስቀመጠ ቢሆንም የልማት ዕቅዱን መነሻ

በማድረግ ተከታታይነት ባለው መልኩ በየዓመቱ ስንት ከተሞች ላይ ክትትል እንደሚያደርግ የማያቅድ በመሆኑ እንዲሁም ግብረ መልስ ለክልሎች መስጠታቸው እንደ በቂ ቆጥረው የሰጡት ምላሽ ላይ ግብረመልስ አሰጣጥ ላይ ለባለቤቱ(ለተግባሪው) በዋናነት ሊሰጥ ስለሚገባ እንዲሁም የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

64.ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት አለመስራት በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ሁሉንም በአገሪቱ ያሉ በደረቅ ቆሻሻ ስርዓት የገቡ ከተሞችን ለይቶ በጋራ እቅድ እንዳይያዝ እንዳይተገበር ስለማድረጉ በምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

65.የከተማ አስተዳደሮች ዝቅተኛውን የአስተዳደር እርከናቸውንና የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ ባሳተፈ መልኩ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ በማዘጋጀት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ክትትል ባለመደረጉ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በባለቤትነት እንዳይተገብሩ እንዲሁም በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዙሪያ የሚፈለገውን ውጤት እንዳያመጣ አድርጓል፡፡

## የቆሻሻ አሰባሰብ፣ የማጓጓዣ ጊዜና ምልልስ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ እና ቋሚ ስለመሆኑ፡

66. ባለሥልጣኑ በመስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ የቆሻሻ አሰባሰብ፣ የማጓጓዣ ጊዜና ምልልስ ለሁለም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ እና ቋሚ ስለመሆኑ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- በድሬዳዋ፣ በሃረሪ፣ አዳማ እና ሻሸመኔ ከተሞች ቆሻሻ የሚሰበስቡ ማህበራት አናሳ መሆናቸውና የቆሻሻ አሰባሰብና ምልልስ ቋሚ እና ተደራሽ እንዳይሆን ያደረገው መሆኑ እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በመስክ ምልከታ ወቅት በድሬዳዋ፣ በሃረሪ እና አዳማ ከተሞች ቆሻሻ በየመንገዱ ተከምሮ የተመለከተ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ የአቃቂ ቃሊቲ የደረቅ ቆሻሻ ቅብብሎሽ ጣቢያ ወደ ረጲ ቆሻሻ ሳይወሰድ ሶስት ዓመት የሆነው እና አካባቢን እየበከለ የሚገኝ መሆኑ፤
- በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 እና 9 ቆሻሻው በወቅቱ የማይነሳ መሆኑ እና በክፍለ ከተማው አንድ የቅብብሎሽ ጣቢያ እንዳለ እና ቆሻሻው በ24 ሰዓት ውስጥ መነሳት ቢኖርበትም በወቅቱ የማይነሳ መሆኑ፤
- በምዕራብ ሀረርጌ ዞን ባሉ 7 ከተሞች የቆሻሻ አሰባሰብ፣ የማጓጓዣ ጊዜና ምልልስ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ እና ቋሚ መሆኑን በተመለከተ የተዘረጋ ስርዓት የሌለ መሆኑን እና ህብረተሰቡ ቆሻሻን በየቦታው እንደሚጥል እና የተደራጁ ማህበራት የሌሉ መሆኑ፤
- በኦሮሚያ የአካባቢ ጥበቃ በ2014 ዓ.ም በተደረገ የክትትልና የቁጥጥር ሪፖርት ላይ ሰበታ፣ አዳማ፣ ሻሸመኔ፣ ቡራዩ፣ ሞጆ፣ ዱከም፣ጣሮ እና ሰንዳፋ የቆሻሻ አሰባሰብ፣ የማጓጓዣ ጊዜና ምልልስ ለሁለም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ እና ቋሚ አለመሆኑ፤

➢ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ያሉ ቢሆንም ባለስልጣኑ በመስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ የቆሻሻ አሰባሰብ፣ የማጓጓዣ ጊዜና ምልልስ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ እና ቋሚ ስለመሆኑ ድጋፍና ክትትል ያላደረገ መሆኑ፤
➢ ባለስልጣኑ ከ2012 ዓ.ም እስከ በ2014 ዓ.ም በከተሞች ላይ ባደረገው ክትትል የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ላይ የተሰማሩ ማህበራት በበቂ ሁኔታ ያልተደራጁ መሆኑን እንዲሁም የደረቅ ቆሻሻ የምልልስ ጊዜ በቂ እና ተደራሽ አለመሆኑ የገለፀ ቢሆንም ለተግባሪ አካላት ግብረመልስ የማይሰጥ መሆኑ፤

በቃለመጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

68.ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፡- ቆሻሻ ሰብሳቢ ማህበራት ከከተሞች በጀት፣ ስፋትና ፍላጎት አንጻር በከተሞች የሚወሰን መሆኑን እና የቆሻሻ አሰባሰባቸው እየተሻሻለ የመጣና ቆሻሻን ለማንሳት የሽግግር ጣቢያዎች ላይ እስኪነሳ ድረስ እንደሚከማች ገልፀዋል፡፡
69.የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ በናሙና ባየናቸው ከተሞች በሀረሪ፣ በድሬዳዋ፣ በጭሮ፣ በአዳማ፣ በሞጆ፣ በሻሸመኔ እና በሃዋሳ ቆሻሻ ሰብሳቢ ማህበራት እጥረት ያላቸው በመሆኑ እና የሽግግር ጣቢያ የሌላቸው በመሆኑ እንዲሁም በአዲስ አበባ የሽግግር(ቅብብሎሽ ጣቢያ) አናሳ በመሆናቸው ለምሳሌ፡- በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ያለ ቢሆንም በወረዳ 1 ብቻ 1ቅብብሎሽ ጣቢያ ያለ በመሆኑ እና ቆሻሻን በአግባቡ የመሰብሰብ ችግር በሰፊው የሚስተዋል በመሆኑ ምላሻቸውን አልተቀበልነውም፡፡
70.ባለስልጣኑ የቆሻሻ አሰባሰብን በተመለከተ የከተማና መሰረተ ልማት ኃላፊነት አድርጎ በመውሰዱ በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ባለስልጣኑ በተሰጠው ሃላፊነት መሰረት ተከታታይነት ባለው መልኩ ድጋፍና ክትትል ላለማድረጉ እንደምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡
71.ባለሥልጣኑ በመስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ የቆሻሻ አሰባሰብ፣ የማጓጓዣ ጊዜና ምልልስ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ እና ቋሚ ስለመሆኑ ድጋፍና ክትትል ባለማድረጉ በከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ እንዲሁም አወጋገድ እና መልሶ መጠቀም ላይ ለማዋል እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት የተሻለ ውጤት እንዳያስገኙ እንዲሁም ቆሻሻ በየመንገዱ ያለአግባብ እንዲጣል፣ የዜጎችን ጤና አደጋ ላይ እንዲወድቅ አድርጓል፡፡

## ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ሊደርስ የሚችል ብክለትን የመከላከያ እርምጃ መወሰዱን ክትትል ስለመደረጉ፣

72.ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ሊደርስ የሚችል ብክለትን የመከላከያ እርምጃ መወሰዱን ክትትል በማድረግ፡ ምልክት የተደረገባቸው ጉድፍ ማጠራቀሚያዎች በየጎዳናው ዳርና በሌሎች የሕዝብ ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲቀመጡ፤ቆሻሻ በሚሰበሰብበት ወቅት ቢያንስ 2

የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ማለትም የሚበሰብስ እና ሊበሰብስ የማይችል ቆሻሻን ማጠራቀም የሚያስችል የተለያየ ከለር ባለው ገንዳ እየተከማቸ ስለመሆኑ፤ የጉድፍ ማጠራቀሚያ ሞልቶ ሳይዝረከረክ ቆሻሻ በየወቅቱ በቆሻሻ ሰብሳቢ ተሸከርካሪዎች መነሳቱን ማረጋገጣቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል::

73. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- <u>ምልክት የተደረገባቸው ጉድፍ ማጠራቀሚያዎች በየጎዳናው ዳርና በሌሎች የሕዝብ ማዘውተሪያ ስፍራዎች ስለ መቀመጥቸው</u>
    - በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ከተሞች በሀዋሳ፣ በአዲስ አበባ፣ አዳማ እና ሻሸመኔ ዋና ዋና አስፋልቶች ላይ ብቻ ምልክት የተደረገባቸው ጉድፍ ማጠራቀሚያዎች በተወሰነ መልኩ ያሉ ቢሆንም በውስጥ ለውስጥ መንገዶች ማጠራቀሚያዎቹ አለመኖራቸው፤ በድሬዳዋ ፣ በሐረር፣ በም/ሐ/ዞን በጭሮ እና በሞጆ ከተሞች በተደረገ የመስክ ምልከታ በየጎዳናው ዳር እና በህዝብ ማዘውተሪያ ስፍራዎች ምልክት የተደረገባቸው የጉድፍ ማጠራቀሚያ እንደሌለ የተመለከትን መሆኑ፤
    - በኦሮሚያ የአካባቢ ጥበቃ በ2013 ዓ.ም በተደረገ የክትትልና የቁጥጥር ሪፖርት ላይ በሱልልታ፣ ሆለታ፣በቡራዩ እና በለገጣፎ ከተሞች ጉድፍ ማጠራቀምያ እንደሌላቸው የተገለፀ መሆኑ፤
    - ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ምልክት የተደረገባቸው ጉድፍ ማጠራቀሚያዎች በየጎዳናው ዳርና በሌሎች የሕዝብ ማዘውተሪያ ስፍራዎች መቀመጣቸውን በ2012 እና በ2013 ዓ.ም ያረጋገጠ ቢሆንም ግብረመልሱ ለተግባሪ አካል (ለከተሞች) የማይልክ መሆኑ እና በ2014 ዓ.ም ይህን በተመለከተ ክትትል ያላደረገ መሆኑ፤
- <u>የሚበሰብስ እና የማይበሰብሱ የደረቅ ቆሻሻዎች ተለይተው ስለመሰብሰባቸው እና የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ሞልተው ሳይዝረከረኩ ቆሻሻዎቸ በወቅቱ ስለመነሳታቸው፡</u>
    - በኦዲቱ በናሙና በታዩ ከተሞች ቆሻሻ የመሰብሰብ አሰራር የተለያየ ሲሆን በሲዳማ ከሆቴሎች ፣ ሪዞርቶች እና አንድ አንድ ተቋማት ፣ በሻሻመኔ ፣ በአዳማ ፣በአዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ፣ ሀዋሳ፣ ሃረሪ ከተሞች በቀጥታ በመኪና/በጋሪ ዙረው በየመኖሪያ ቤቱ ቆሻሻ የሚሰበስቡበት አካሄድ ያላቸው ቢሆንም ከአንዳንድ ቦታዎች በስተቀር የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ አገልግሎት የሌለ መሆኑ፤ ገንዳዎች ባሉበት አካባቢም የሚበሰብስና የማይበሰብስ በሚል የተለየ አለመሆኑን እንዲሁም የጉድፍ ማጠራቀሚያ ላይ የተጠራቀሙት ቆሻሻ ሞልቶ የሚዝረከረክ ሁኔታ የታየ መሆኑ፤
    - በባህር ዳር፣ ደሴ፣ ጎንደር፣ቴፒ እና ቦንጋ ከተሞች ምንም አይነት ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ እንዲሁም ጊዜያዊ ቆሻሻ ማቆያ ስፍራ የሌለ መሆኑን እና ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ ሁሉም የፕላስቲክ አይነቶች ተቀላቅለው እና ምንም አይነት የመለየት ስራ እየተከናወነ አለመሆኑ በባለስልጣኑ የ2013 ዓ.ም ለከተሞች በተደረገ ክትትል ሪፖርት የተገለፀ መሆኑ፤
    - በኦሮሚያ የአካባቢ ጥበቃ በ2013 ዓ.ም በተደረገ የክትትልና የቁጥጥር ሪፖርት ላይ በሱልልታ፣ ሆለታ፣ በቡራዩ እና በጣፎ ደረቅ ቆሻሻ

የሚበሰብስና የማይበሰብስ ተብሎ ተልይቶ የማይቀመጥ መሆኑ እና በየሰፈሩ ቆሻሻዎች የሚዝረከረኩ መሆናቸው የገልፁ መሆኑ፤

- በአገሪቱ ባሉ ከተሞች በማህበረሰቡ ዘንድ በአቅራቢያቸው የተሰበሰበውን ቆሻሻ(የፕላስቲክ ቆሻሻን ጨምሮ) የማቃጠል ልምድ(ለምሳሌ-በየዓመቱ የሚከናወነው ሕዳር ሲታጠን) በሰፊው መኖሩ፤




ፎቶ ቁጥር 1፡ ደረቅና ፕላስቲክ ቆሻሻ አንድላይ የማቃጠል ልምድ እንዳለ የሚያሳይ

## የቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራዎችን በተመለከተ፡

- የኦዲት ቡድኑ በሐረር፣ሃዋሳ፣ ጭሮ፣ አዳማ፣ ሞጆ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሻሸመኔ ከተሞች ባደረገው የመስክ ምልከታ እና በባለስልጣኑ በተደረገ የክትትል ሪፖርት (በባህርዳር፣ ደሴ ፣ጎንደር እና ቦንጋ) ማስረጃዎች መሰረት የሚገኙ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች (Sanitery land fill) ሳይሆኑ ክፍት ስፍራ ላይ የሚገኙ፤ የሚበሰብሱ እና የማይበሰብሱ ቆሻሻዎች ተለይተው ያልተቀመጡባቸው፣ ቆሻሻው በአግባቡ የማይጣል በመሆኑ እሳት የሚያስነሱ መሆናቸው፣ ከህብረተሰቡ መኖሪያ ቤቶች ተገቢውን ርቀት ያልጠበቁ፣ ከቆሻሻዎቹ የሚመነጩ መርዛማ ፍሳሾች በአካባቢው በሚገኙ የወንዝ ተፋሰሶች ጋር የሚቀላቀሉ መሆኑና በወንዙ መስኖ የሚጠቀሙ ገበሬዎች(ገበሬዎቹ የሚያመርቱትን ምርት ለሚጠቀሙ ማህበረሰብ የሚያቀርቡ) እና በየቦታው ከተጣሉ ቆሻሻ ፌስታል የሚበሉ እና ከወንዙ የሚጠጡ እንስሳትን ጤና ጉዳት ላይ የጣሉ መሆኑ፤



**ፎቶቁጥር፡2 የድሬዳዋ ክፍት የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የሚበሰብሱ እና የማይበሰብስ ተለይቶ የማይቀመጥ መሆኑ የሚያሳይ**



**ፎቶ ቁጥር 3፡ የአዲስ አበባ ረጲ ክፍት የቆሻሻ ማስወገጃ ከህብረተሰቡ መኖሪያ ርቀት ያልጠበቀ እና ፍሳሹ ከወንዝ የሚቀላቀል መሆኑን የሚያሳይ**



**ፎቶ-ቁጥር 4፡ በቡራዩ ከተማ- በየቦታው ከተጣሉ ቆሻሻ ፌስታል የሚበሉ እንስሳት ለጤና ጉዳት እየተጋለጡ መሆኑን የሚያሳይ**

- በኦሮሚያ የአካባቢ ጥበቃ በ2013 ዓ.ም በሱልልታ፣ ሆለታ፣በቡራዮ እና በለገጣፎ እንዲሁም በ2014 ዓ.ም ሰበታ፣ አዳማ፣ ሻሸመኔ፣ ሞጆ፣ ዱከም፣ ለገጣፎ ከተሞች በተደረገ የክትትልና የቁጥጥር ሪፖርት ደረቅ ቆሻሻ የሚጣሉት ክፍት በሆነ ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ መሆኑን እና ቆሻሻ ማስወገጀ ክፍት ቦታው ለህብረተሰቡ በጣም የተጠጋ መሆኑን እና ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (Sanitery land fill) የሌላቸው መሆኑን የሚገልፅ መሆኑ፤

- የአገሪቱ ዋና ከተማ በሆነችው በአዲስ አበባ የሚገኘውን ረጲ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታን በተመለከተ፡
    - የቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራው ከ50 ዓመት በላይ የሆነው እና በአሁኑ ሰዓት ከአቅም በላይ ቆሻሻ የያዘ መሆኑ፤
    - ከ 30-40 ሜትር ተራራ(የቆሻሻ ክምር) ወደ ላይ የፈጠረ መሆኑን፤ ተራራውን በመጠኑ ለመጠቅጠቅ ያሉት ሎደሮች አብዛኞቹ የተበላሹ መሆናቸው እና አንድ ዶዘር የአዲስ አበባ ከተማ የፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ተከራቶ የሰሩ ያለ ቢሆንም በቂ እንዳልሆነ፤
    - የቆሻሻ ክምሩ እየጨመረ መሆኑ እና በራሱ ጊዜ እሳት የሚነሳበት ሁኔታዎች እየተፈጠረ መሆኑን እና እሳቱ ለማጥፋት በኤክስካባተር በሚያዳፍኑበት ወቅት ቆሻሻው የሚደረመስ በመሆኑ የአካባቢው ማህበረሰብ ስጋት የፈጠረበት መሆኑን፤

- ከረጲ ቆሻሻ ማስወገጃ ክፍት ስፍራ አጠገብ ረጲ ኤሌክትሪክ ማመንጫ በ2012 ዓ.ም ጀምሮ ከቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ብረቶች፣ ማይካ ኤሌትሮኒክስ፣ ሀይላንዶች እንዲለዩ በማድረግ ፌስታሎችን ከሚበሰብስ ቆሻሻ ጋር ኤሌትሪክ የማመንጨት ስራ የሚከናወን ሲሆን ፕሮጀክቱ ሲቋቋም በሰዓት 50 ሜጋ ዋት ለማምረት የተጠና ቢሆንም ከ3 ወር በፊት 13 ሜጋ ዋት ብቻ ያመርት እንደነበረ ነገር ግን ኤሌክትሪክ ማመንጨት ካቆመ 3 ወር የሆነው መሆኑ፤ ሆኖም ይህንን በተመለከተ በባለስልጣኑ የሚደረግ ክትትልና ድጋፍ አለመኖሩ የላንድ ፊል አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የተገለፀ መሆኑ፤

➢ በባለስልጣኑ በ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ደብረ ታቦር ፣ እንጅባራ ፣ ወላይታ ሶዶ ፣ አርባ ምንጭ ፣ ባሌ ሮቤ ፣ ጅግጅጋ ፣ ሀረር እና ድሬደዋ ከተሞች ፣በ2013 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በጅማ፣ ጭሮ፣ በደሌ፣ ቦንጋ፣ ሚዛን- ቴፒ፣ ጅግጅጋ፣ ቶጎጫሌ፣ አሳይታ፣ አዋሽ ሰባት፣ ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ደሴ፣ ሀረር እና ድሬደዋ፤ በ2014 በጀት አመት የደረቅ ቆሻሻ ዘገባ ላይ አዳማ፣ ቢሾፍቱ፣ አሰላ፣ ቡሌሆራ፣ ዲላ፣ ይርጋጨፌ፣ አዋሳ፣ ሻሸመኔ፣ ሳውላ፣ አርባምንጭ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ጅንካ፣ ኮንሶ/ካራት፣ ድሬደዋ፣ ሀረር፣ ጭሮ፣ ጅጅጋ እና ገለምሶ ከተሞች ባደረገው ክትትል ከተሞቹ የሚመነጩትን ደረቅ ቆሻሻ በአግባበቡ አለመሰብሰብ፣ ቆሻሻን መልሶ መጠቀም የሚያስችል ስርዓት ያለመኖር ፣ ቆሻሻን ወደ ቀልዝ(ኮምፖዝ) የመቀየር ስራ በሁሉም ከተሞች አለመጀመር ፣ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ አያያዝ ጉድለት ፣ ቆሻሻን ከምንጩ የመለየት ሥራ ዝቅተኛ መሆን ፣ የማስወገጃ ቦታዎች ክፍት መሆን ችግሮች ያላቸው መሆኑ የተገለፀ መሆኑን፤

በቃለመጠይቅ፣ በመስክ ምልከታ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

74.ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት መልስ፡- በከተሞች የቆሻሻ አያያዝ ላይ የገንዳ ስርዓት በአብዛኛው አነስተኛና መካከለኛ ከተሞች ካለው ጥቅም አንጻር ጉዳቱ ስለሚያመዝንና በቆሻሻ አያያዝ የህዝብ ቅሬታ፣ የውሾችና ሌሎች የቤት እንስሳት መዋያ በመሆኑና ጠቃሚ ነገሮችን በሚለቅሙ ሰዎች የቆሻሻ መበተን ችግሮች ስለሚከሰቱ፤ በነዋሪዎች መካከልም ከመቀመጡ አንጻር አበረታች ባለመሆኑ ምክንያት አብዛኛዉ ከተሞች ስርዓቱ እንዲቀር ማድረጋቸው ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት ሆኖም በተለያዩ ከተሞች የቆሻሻ ማጠራቀሚያ/ደስት ቢን የሌለ መሆኑንና ማጠራቀሚያው ባለባቸውም ከተሞችም በቂ በሚባል ደረጃ የሌለ መሆኑን ፤ ይህንን በተመለከተ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ የመስክ ክትትልና ቁጥጥር ቼክሊስት አካቶ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ክትትልና ቁጥጥር እንደሚያደርግ ከቼክ ሊስትና ከተዘጋጁ ዘገባዎች መረዳት የሚቻል መሆኑን፤ የቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራዎች በተመለከተ በአዲስ አበባ ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራና ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር ጉዳቱን ለመቀነስ የዌስት ቱ ኢነርጂ ተቋም ማቋቋምና በከተማው የሚመነጨውን ቆሻሻ ብክለት ለመቀነስ እንደ መፍትሄ የተቋቋመ ስራ ሲሆን በአሁኑ ወቅትም ኃይል የማመንጨት ስራ ባይሰራም ከዲዛይኑ ጀምሮ የአየር ብክለትን በሚቀንስ መልኩ በአውሮፓ ስታንዳርድ የተሰራ መሆኑን እና

ቆሻሻ በከፍተኛ ሙቀት ስለሚያቃጠል የአየር ብክለት በሚቀንስ መልኩ በቀን 1200 ቶን ቆሻሻ እያቃጠለ የሚገኝ ስለመሆኑ እና የተለያዩ ስራዎችንም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ እየሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ(ቦታ) የሚበሰብስና የማይበሰብስ በሚል የሚለይበት አግባብ የሌለ በመሆኑ ጽንሰ ሃሳቡ አግባብነት የሌለው መሆኑ ገልፀዋል፡፡

75. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ አብዛኛው ከተማ የቆሻሻ አያያዝ ስርዓቱን በምን እንደቀየሩት እና የገንዳ ስርዓት ከጥቅሙ ጉዳቱ ማመዘኑ የታወቀበት በጥናት የተደገፈ(በሃገር ደረጃ የተገመገመበት) እንዲሁም ክትትል ያደረጉበትን ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ፤ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ/ደስት ቢን መኖሩ ክትትል ያረገበት በ2013 ዓ.ም ለከተሞች ባደረገው ክትትል ብቻ መሆኑን፣ ረጂ የደረቅ ቆሻሻ የኤሌትሪክ ማመንጫ በተመለከተ ቆሻሻ ሲያቃጥል የአየር ብክለት በሚቀንስ መልኩ የሚያቃጥል መሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የሌለ በመሆኑ፤ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራዎች የሚበሰብስ እና የማይበሰብስ አለመለየት ቆሻሻውን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል አስቸጋሪ ሁኔታዎች እየፈጠረ በመሆኑ እንዲሁም በአካባቢ፣ በሰው እና በእንስሳት ላይ ጉዳት እያደረሰ በመሆኑ ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡
76. የግንዛቤ ክፍተት መኖር እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር አናሳ መሆን በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው የከተማ አስተዳደሮች ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ሊደርስ የሚችል ብክለትን የመከላከያ እርምጃ ላለመውሰዳቸው እንደ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡
77. የከተማ አስተዳደሮች ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት እና ቆሻሻን ከምንጩ የመለየት ሥራ ዝቅተኛ መሆን ችግሮች ያለበት በመሆኑ ቆሻሻ ከምንጩ እንዳይቀንስ የሚያደርግ ሲሆን የማስወገጃ ቦታዎች ክፍት መሆንና ዘመናዊ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንዲኖር ክትትል በማድረግ ግብረመልስ ባለመስጠቱ በየከተማው ያለው የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ የአካባቢ ብክለት በመጨመር በማህበረሰቡ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠረ ይገኛል፡፡

## በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች የጤንነትና ደህንነት መጠበቂያ በተመለከተ

78. ባለስልጣኑ በመስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ የሚገኙ በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች የራስ ጤንነትና ደህንነት መጠበቂያ እንዲሁም የስራ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ስለመኖራቸው ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡
79. ይሁን እንጂ
    - በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ሃረሪ፣ ድሬዳዋ፣ ጭሮ፣አዳማ፣ሞጆ ሻሸመኔ ሀዋሳ እና የአዲስ አበባ የፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በታዩ ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ የሚገኙ በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ስራ ላይ ለተሰማሩ የራስ ጤንነትና ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች እንዲሁም የስራ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ ለፅዳት ሰራተኞች የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች በተወሰነ መልኩ የቀረቡላቸው ቢሆንም ለሁሉም ሰራተኞች በተከታታይነት የማይቀርብ መሆኑ እንዲሁም በተወሰነ መልኩ የሚቀርብላቸውን የራስ ጤንነትና

ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች ላይ ሰራተኞቹ የመጠቀም ክፍተት ያለባቸው መሆኑ፤

- ባህር ዳር፣ ደሴ፣ ጎንደር፣ቴፒ እና ቦንጋ በከተሞች የስራ ደህንነትን በተመለከተ ማህበራቱም ይሁኑ የከተማ አስተዳደሩ አስፈላጊ የሆኑትን የስራ ደህንነት መጠበቂያ እንዲሟላ አለማድረጋቸው ከየባለስልጣኑ የክትትል ሪፖርት የተከለሰ መሆኑ፤

በቃለመጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

80. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፡- የተጠቀሱትን ነባራዊ ሁኔታዎች በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር የተለየ ክፍተት መኖሩን እንዲያስተካክሉ ለሚመለከተው አካል ማሳወቃቸውን ገልፀዋል፡፡
81. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ የክትትል ሁኔታው በቂ አለመሆኑ እና የክትትል ውጤቶች ላይ ተመስርቶ የሚመለከታቸው አካላት ስለመተግበራቸው እስከመጨረሻ ባለማረጋገጣቸው ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡
82. የስራ ደህንነት መጠበቂያ እና ስራን ለማቀላጠፍ የሚያግዙ መሳሪያዎች ለሰራተኞቹ ስለመድረሱ የተጠናከረ ክትትል አለማድረግ እና ለሰራተኞቹ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በቅንጅት አለመከናወኑ በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች ለጤና እና ስራ የሚያስፈልጓቸው ግብዓቶች ተሟልተው ላለመቅረባቸው እና ሰራተኞቹ ስራ በሚሰሩበት ወቅት የስራ መሳሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም ላይ ክፍተት ስለመታየቱ እንደ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡
83. በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ስራ ላይ ለተሰማሩ የራስ ጤንነትና ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች እንዲሁም የስራ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥና ወጪን ለመቀነስ ለሰራተኞች የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ተሟልተው ባለመቅረባቸው ሰራተኞቹን ለጤና ጉዳት ሊዳርጋቸው ይችላል፡፡

## የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ቁጥጥር በማድረግ እርምት እርምጃ ስለመወሰዱ፡

84. ባለስልጣኑ በፌደራል፣ በክልል እና በከተማ አስተዳደሮች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ቁጥጥር ላይ የተሰሩ ዘገባዎችን በመመርመር በከተሞች አካባቢን በሚበክል አካል እና ጉልህ አሉታዊ ተጽዕኖ በሚያደርሱት ላይ ተጠያቂነትን ለማስፈን ወደ ፍትህ አካላት የሚቀርቡትንና አስተዳደራዊ እርምት የሚወሰዳባቸው ጉዳዮች ላይ ሊወስን፣ ተግባራዊነቱን ሊከታተል፣ ሊደግፍ፣ ሊመራና ሊያስተዳድር ይገባል፡፡
85. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡
   - ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ቁጥጥር ላይ በባለድርሻ አካላት የተሰሩ ዘገባዎችን በመቀበል የሚመረምርበት አሰራር የሌለው መሆኑን እንዲሁም ባለስልጣኑ በራሱ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ቁጥጥር ላይ የሚሰራቸው የተወሰኑ ዘገባዎች ቢኖሩም ወደ ፍትህ አካላት የሚቀርቡትንና አስተዳደራዊ የእርምት እርምጃ የሚወሰድባቸው ጉዳዩች ተለይተው ስራዎች አለመሰራታቸው፤

- በናሙና በታዩ ክልሎች እና ከተሞች፣ የኦሮሚያ የአካባቢ ባለስልጣን፣ በአዲስ አበባ ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ክፍለ ከተማ የፅዳት አስተዳደር ፅ/ቤት ፣ አቃቂ ክፍለ ከተማ የፅዳት አስተዳደር ጽ/ቤት ፣ በድሬዳዋ፣ በሐረር እና በጭሮ ከተማ አካባቢን የሚበክል አካል አካባቢው ላይ ባደረሰው ብክለት ልክ ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲከፍል የማይደረግ እና ጉልህ አሉታዊ ተጽዕኖ በሚያደርሱት ላይ ተጠያቂነትን የማስፈን ስርአት ያልተዘረጋ መሆኑን የገለፁ መሆኑ፤
- ባለሥልጣኑ በከተሞች ማንኛውም አካባቢን የሚበክል አካል አካባቢው ላይ ባደረሰው ብክለት ልክ ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲከፍል የማድረግ እና ጉልህ አሉታዊ ተጽዕኖ በሚያደርሱት ላይ ደግሞ ተጠያቂነትን እንዲሰፍን የሚያደርግ ስርአት በመዘርጋት እየተገበሩ ስለመሆናቸው ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፤

በቃለመጠይቅ፣ በመስክ ምልከታ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

86. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት መልስ፡- ፍትህ አካላት የሚቀርቡና አስተዳደራዊ እርምት የሚወሰድባቸው ጉዳዮች ተለይተው እርምጃ ለመውሰድ የህግ ማዕቀፍ ድጋፍ እንደሌለው እና በረቂቅ አዋጅ ምላሽ እንድያገኝ የተደረገ መሆኑ ገልፀዋል፡፡
87. የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎች አለመኖራቸው እና ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቅንጅት ስራው የላላ በመሆኑ በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ቁጥጥር ላይ ወደ ፍትህ አካላት የሚቀርቡትንና አስተዳደራዊ የሚወሰዳባቸውን ጉዳዮች ተለይተው ህጉን በተላለፉ አካላት ላይ ቅጣት እንዲፈፀም ላለማስቻሉ እንደ ምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡
88. ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ቁጥጥር ላይ ወደ ፍትህ አካላት የሚቀርቡትንና አስተዳደራዊ የሚወሰዳባቸውን ጉዳዮች ተለይተው ህጉን በተላለፉ አካላት ላይ ቅጣት እንዲፈፀም ባለመደረጉ የተጠያቂነት ስሜት እንዳይኖርና ሌሎች ሰዎችም ከተቀጪዎች እንዳይማሩ አድርጓል።

## የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና የፕላስቲክ አምራች ፈቃድ አሰጣጥ በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት ስለመዘርጋቱ፡

89. ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት በተመለከተ ከዘርፉ መ/ቤቶች፣ ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግና የከተማ አስተዳደሮች እና ክልሎች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህግ ተከባሪነት ደረጃን የሚገልፅ የቁጥጥርና ክትትል ሪፖርት መዘጋጀቱን ሊከታተል ፣ ሊቆጣጣር እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
90. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡
    - በኦዲቱ ወቅት በናሙና ካየናቸው የክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤቶች እና ከተሞች የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የቁጥጥር ስርዓት

ውጤታማነት በተመለከተ የአዲስ አበባ፣ የሃረሪ፣ ድሬዳዋ፣ጭሮ፣ ሃዋሳ፣ሻሸመኔ፣ ሞጆ እና አዳማ ከተሞች ለየክልላቸው የአካባቢ ጥበቃ እና ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማይልኩ መሆናቸው እና ባለስልጣኑ የከተሞች የአፈፃፀም ሪፖርታቸው ክትትል የማያደርግ መሆኑ፣ ወጥ የሆነ የሪፖርት አቀራረብና ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት የላላ መሆኑ፤

- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን በ2014 ዓ.ም ማጠቃለያ ሪፖርት ለከተሞች በተደረገው ክትትልና ቁጥጥር በባለድርሻ አካላት መካከል ተቀናጅቶ የማይሰሩ መሆናቸው፤
- የባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህግ ተከባሪነት ደረጃን የሚገልፅ የቁጥጥርና ክትትል በተመለከተ ከከተሞች ሪፖርት የማይቀበል መሆኑ፤

በቃለመጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

91.ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት፤- ባለስልጣኑ ከከተሞች ጋር በሪፖርት የሚገናኝበት አሰራር የሌለ መሆኑን ሪፖርት በተዋረድ ተጠሪነት ላላቸው አካላት የሚቀርቡ መሆኑን ሆኖም በተለያዩ ጊዜያት የከተሞችን የአፈጻጸም ደረጃ የተቀበለበት ማስረጃ ስላለ ማቅረብ እንደሚችሉ ገልፀዋል፡፡

92.ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ በ2012 እና በ2014 ዓ.ም የተወሰኑ ሪፖርት ማስረጃዎች ከክልል የአካባቢ ጥበቃዎች የተቀበሉ መሆኑና በ2013 ዓ.ም ምንም አይነት ሪፖርት ከክልል እና ከተማ መስተዳደሮች ያልተቀበሉ በመሆኑ ይህም ተከታታይነት ባለው መልኩ ሪፖርቶችን የማይቀበሉ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ እንዲሁም ባለስልጣኑ የከተሞች የእቅድ አፈፃፀም ደረጃ የሚከታተልበት ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ ምላሻቸውን አልተቀበልነውም፡፡

93.በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዙሪያ ትኩረት ሰጥቶ ያለመስራት በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ላለመስራታቸው እንደ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

94.በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ባለመሰራቱ ሁሉም የሚመለከተው ባለድርሻ አካል በተቀናጀ ሁኔታ ስራቸውን እንዳይሰሩ፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት ላይ ሊመዘገብ የሚገባው ለውጥ እንዳይመጣ፣ ወጥ የሆነ ሃገር አቀፍ የቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ እንዳይኖር እና በዘርፉ መ/ቤቶች፣ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች መልካም ተሞክሮዎችን እርስ በእርስ መጋራት እንዳይቻል አድርጓል።

## በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት መስክ ኢንቨስትመንት ስለመስፋፋቱ፡

95.ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት መስክ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል::

96.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- በናሙና በተመረጡ የአዲስ አባባ ከተማ የፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ላይ የሚሳተፉ 5 ባለሀብቶች ቢኖሩም ነገር ግን

በቂ በሚባል ደረጃ አለመሆኑ፤ በሐረሪ፣ ድሬዳዋ፣ ሻሸመኔ፣ ሀዋሳ እና ሞጆ በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት መስክ ኢንቨስትመንት ከሚበሰብስ ቆሻሻ ኮምፖዝ በመስራት ስራ ላይ) በጅምር ደረጃ እንዳለ፤ በጭሮ ከተማ የሚሰራ የኢንቨስትመንት ስራ የሌለ መሆኑ፤

- በባለስልጣኑ የመስክ ክትትል ዘገባ፦
    - በ2013 ዓ.ም፦
        - በደሴ ከተማ ቆሻሻን ወደ ቀልዝ የመቀየር ስራ የተጀመረ ቢሆንም በበቂ ሁኔታ እየተጓዘ አለመሆኑን፤
        - ቴፒ እና ቦንጋ ከተሞች ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል እየተሰራ ያለ ተግባር የሌለ መሆኑን፤
    - 2014 ዓ.ም፦
        - አሰላ፣ ቡሌሆራ፣ ይርጋጨፌ፣ ሳውላ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ኮንሶ/ካራት፣ ጅጅጋ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል እየተሰራ ያለው ስራ አነስተኛ መሆኑ፡

በቃለመጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

97. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት መልስ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999 ኢንቨስትመንት የማስፋፋት ኃላፊነት የተሰጠው ለከተማ አስተዳደሮች መሆኑን ከአዋጁ ማረጋገጥ እንደሚቻል ሆኖም በህግ በተጣለባቸው ኃላፊነት መሰረት እየሰሩ ያለመሆኑን በክትትልና ቁጥጥር ወቅት ያረጋገጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
98. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት መስክ በክልሎች እና ከተማ መስተዳደሮች ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውን ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትል በማድረግ ግብረ መልስ ያልሰጡ እና ድጋፍ ያላደረጉ በመሆኑ ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡
99. ባለስልጣኑ ዜጎች መዋዕለ ንዋያቸውን ደረቅ ቆሻሻ ላይ እንዲያፈሱ የሚጋብዝ አሰራር ባለመዘርጋቱና ይህን በተመለከተ ግንዛቤ ማስጨበጫ ባለማዘጋጀቱ በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት መስክ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ላለመሆኑ እንደ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡
100. የከተማ አስተዳደሮች በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት መስክ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ባለመደረጉ የደረቅ ቆሻሻ መስክ በመንግስትና በጥቂት ባለሃብቶች ብቻ እንዲሰራ፣ ቆሻሻን መልሶ መጠቀም ላይ በሚፍልግው መጠን እንዳይሰራ አድርጓል።

**በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ ስልጠና ስለመሰጠቱ፡**

101. ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት በተመለከተ ለዘርፉ መ/ቤቶች፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

102. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት በተመለከተ በናሙና በተመረጡ ከተሞች የአዲስ አበባ ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ ድሬዳዋ፣ ሲዳማ፣ሻሻመኔ፣አዳማ፣ ሞጆ፣ ሐረር እና ምዕ/ሐ/ዞን ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣኖች፣ አልፎ አልፎ ስልጠናዎች የሚሰጡ ቢሆንም የሚሰጠው ስልጠና ባለሙያ ያላካተተና ለኃላፊዎች ብቻ የሚሰጥ እንዲሁም በቂና ተከታታይነት የሌለው መሆኑ፣
- በአዲስ አባባ ከተማ የፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻን በተመለከተ አልፎ አልፎ የሚሰጣቸው ስልጠና መኖሩ የገለፁ ቢሆንም ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑ፣
- በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ፅ/ቤት እና የፅዳት አስተዳደር ፅ/ቤት ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር ምንም ዓይነት ቅንጅታዊ አሰራር የሌላቸው መሆኑ እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን በ2012 ዓ.ም በፊት አልፎ አልፎ ስልጣና ይሰጣቸው እንደነበር ከ2012 ዓ.ም ወዲህ ግን ስልጠና ሰጥቷቸው እንደማያውቅ የገለፁ መሆኑ፣
- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን በ2014 ዓ.ም ማጠቃለያ ሪፖርት የተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ ስርዓትን በተመለከተ ለአመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት አቅዶ ያልተከናወነ መሆኑ፣
- የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በ2005 ዓ.ም ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኢንዱስትሪ ዘርፎች ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች መሰረታዊ የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ማምረቻ ፋብሪካን ጨምሮ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ሰነዶችን የማረጋገጥ ኃላፊነትን በውክልና ሲሰጣቸው የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ምርምርና ውሳኔ አሰጣጥ የክህሎት ማጎልበቻ ስልጠና ለኢንዳስትሪ ሚኒስቴር የመስጠት ኃላፊነት ቢኖርበትም ያልሰጠ መሆኑ፣
- ባለስልጣኑ ከ2012 -2014 ዓ.ም ስልጠና የሰጠበት ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ፣

በቃለመጠይቅ፣ በመስክ ምልከታ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

103. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፡- ባለፉት ሁለት ዓመታት የኮቪድ 19 በሽታ በመከሰቱ ምክንያት ሰዎችን ሰብስቦ ማሰልጠን ያልተቻለ መሆኑን ሆኖም ከዛ በፊት ባሉት አመታት ተከታታይ ስልጠናዎች የሰጡበትን ማስረጃ ያቀረቡ

መሆኑን እንዲሁም የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ስልጠናዎችን ለከተማ ማዘጋጃዎች እየሰጡ በመሆኑ ስልጠናዎችን ያልሰጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

104. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ ያቀረቡት ማስረጃ ተከታታይ ስልጠና ስለመስጠታቸው የማያመለክት በመሆኑ እና የኮቪድ 19 እገዳዎች ከተነሳ በኃላ እስከ 2014 ዓ.ም ስልጠና ያልሰጡ በመሆናቸው እንዲሁም በሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሰጡ ያሏቸውን ስልጠናዎች ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት በተመለከተ ለዘርፉ መ/ቤቶች፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ስለመሰጠታቸው ያረጋገጡበት ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ እና ባለስልጣኑ ከተጣለበት ኃላፊነት የማያስቀሩ በመሆኑ ምላሻቸውን አልተቀበልነውም፡፡

105. ባለስልጣኑ በሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሰጡ ባሏቸው ስልጠናዎች ምክንያት የራስን ሃላፊነት አለመወጣት በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ ለሚመለከታቸው አካላት ተከታታይ ስልጠና ላለመሰጠቱ እንደ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

106. ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ ለሚመለከታቸው አካላት ተከታታይ ስልጠና ባለመሰጠቱ እና የሚሰጡ ስልጠናዎችም ለባለሙያዎች የሚሰጡ ባለመሆናቸው የባለሙያዎችን አቅም መገንባትና ማጎልበት እንዳይቻል፣ የሚመለከታቸው ተግባሪ አካላት ስለ ዘርፉ በቂ ግንዛቤ እንዳያገኙ እንዲሁም የስራ ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው አድርጓል።

## በደረቅ ቆሻሻና ፕላስቲክ ምርቶች ዙሪያ ዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን በመውሰድ ተግባራዊ ስለመደረጋቸው፡

107. ባለስልጣኑ በደረቅ ቆሻሻና ፕላስቲክ ምርቶች ዙሪያ ዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን በመውሰድ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

108. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- በናሙና በታዩ 3 ክልሎች እና 2 ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ 11 የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እና 5 መዘጋጃ ቤቶች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና ፕላስቲክ ምርቶች ዙሪያ ዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮችን በመውሰድ ያልተገበሩ መሆኑን እና በባለስልጣኑም ዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን አስመልክቶ ያደረሳቸው ተሞክሮ የሌለ መሆኑን ገልዋል፤

109. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ፡- በደረቅ ቆሻሻ ዙሪያ ከጋሊ መልካም ተሞክሮዎች መውሰዳቸው እና ማስረጃ እንደሚያቀርቡ ነገር ግን ወደ ታች ወርዶ ወረዳዎች ተግባራዊ በማድረግ ላይ ክፍተቶች እንዳሉ ኔክሲል ከፕላስቲክ ኮዳ ላይ እንዲሁም ማስተርባጅ የፕላስቲክ መልሶ መጠቀም መጠንን የቀነሰው መሆኑ ተጠንቶ ውጤቱ የተተገበረው በዓለም አቀፍ ልምድ መሆኑን እና በረቂቅ አዋጁ ስስ የፕላስቲክ ከረጢት ከገበያ እንዲወጣ የሚለው ሃሳብ እንዲካተት የተደረገው ከአለም አቀፍ ተሞክሮ ተወስዶ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

110. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ ከአለም አቀፍ ተሞክሮዎች የወሰዱባቸውን ማስረጃዎች ያላቀረቡ በመሆኑ ምላሻቸውን አልተቀበልነውም፡፡

111. ባለስልጣኑ መልካም ተሞክሮ እንዲቀስሙ የላካቸውን ኃላፊዎች/ባለሙያዎች የወሰዱትን ተሞክሮዎች ለመተግበር የሚያስችል አሰራር የሌለው በመሆኑ በኦዲቱ እንደ ክፍተት ለተወሰደው በደረቅ ቆሻሻና ፕላስቲክ ምርቶች ዙሪያ ዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን በመውሰድ እስከታች ድረስ ላለመተግበሩ እንደ ምክንያትነተ ሊወሰድ ይችላል፡፡
112. ባለስልጣኑ በደረቅ ቆሻሻና ፕላስቲክ ምርቶች ዙሪያ ዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን በመውሰድ ባለመተግበሩ በደረቅ ቆሻሻና ፕላስቲክ ምርቶች ዙሪያ የተሻለ ለውጥ እንዳይመጣ እና ሀገሪቱ በሁሉም ማሕበረሰብ የሚተገበር የተቀናጀና የተደራጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እንዳይኖራት አድርጓል።

# ክፍል ሶስት

## *መደምደሚያ*

113. የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የፕላስቲክ ምርቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት ሲገመገም የሚከተሉት ግድፈቶችና ጉድለቶች ተገኝቷል

- ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999 በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ደንቦች እና መመሪያዎች አላዘጋጀም፤ ይህን አዋጅ ለማሻሻል (በ2012 ዓ.ም) እንዲሁም በ1989 ዓ.ም የወጣውን የአካባቢ ፖሊሲን ለማሻሻል (በ2013 ዓ.ም) በረቂቅ ደረጃ አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም፤ ፀድቆ ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትል አላደረገም፡፡
- ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህጎችና ደረጃዎች ተፈጻሚነት ላይ ያሉ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ ሃሳቦችን ወደ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲወርድ እንዲሁም የቁጥጥር ዘርፉን ለማሳደግና ለማፋጠን የሚረዳ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል እንዲቀረፅ አላደረገም፡፡
- ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ዝቅተኛውን የአስተዳደር እርከናቸውንና የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ ባሳተፈ መልኩ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀታቸውንና ተግባራዊ ማድረጋቸውን ክትትል አላደረገም፡፡
- ባለሥልጣኑ በከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣አጓጓዝ እንዲሁም አወጋገድ እና መልሶ መጠቀም ላይ ለማዋል እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት የተሻለ ውጤት እንዲያስገኙ እንዲሁም ቆሻሻ በየመንገዱ ያለአግባብ እንዳይጣል በመስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ የቆሻሻ አሰባሰብ፣ የማጓጓዣ ጊዜና ምልልስ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ እና ቋሚ ስለመሆኑ ተከታታይነት ያለው ክትትል በማድረግ ድጋፍ አላደረገም፡፡
- ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ሊደርስ የሚችል ብክለትን የመከላከያ እርምጃ እንዲወስዱ እና ዘመናዊ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንዲኖር ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትል አላደረገም፡፡
- ባለስልጣኑ በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ስራ ላይ ለተሰማሩ የጽዳት ሰራተኞች ለጤና ጉዳት እንዳይጋለጡ ለማድረግ የራስ ጤንነትና ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች እንዲሁም የስራ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ ለሰራተኞች የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ተሟልተው ስለመቅረባቸው በቂ ክትትል

አላደረገም፤ ክትትል ባደረገባቸው ከተሞች ግብረ መልስ ለክልል የሚልክ ቢሆንም ወደ ተግባሪው አካል መድረሱን እና ተግባራዊ መደረጉን የሚከታተልበት አሰራር የለውም፡፡

- ባለስልጣኑ ማንኛውም ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል የልማት ፕሮጀክቶት ባለቤት ወደ ትግበራ ከመግባቱ በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ በማካሄድ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ፈቃድ ማግኘቱን እንዲሁም በሚመለከታቸው የዘርፍ መ/ቤቶች የተሰጡ የአካባቢና የማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ የይሁንታ ፈቃዶች በህጉ መሠረት እየተገበሩ መሆናቸውን አላረጋገጠም፡፡
- ባለስልጣኑ የተጠያቂነት ስሜት እንዲኖርና ሌሎች ሰዎችም ከተቀጪዎች እንዲማሩ ለማድረግ እንዲቻል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ቁጥጥር ላይ ወደ ፍትህ አካላት የሚቀርቡትን እና አስተዳደራዊ እርምት የሚወሰድባቸውን ጉዳዮች ተለይተው ህጉን በተላለፉ አካላት ላይ ቅጣት እንዲፈፀም አላደረገም፡፡
- ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ቆሻሻን ጨምሮ የደረቅ ቆሻሻ ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በጥናት እንዲደገፍ በማድረግ ለሚመለከታቸው አካባቢ አያያዝ መ/ቤቶች እና ህብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲፈጠር አላደረገም፡፡
- ባለስልጣኑ ውፍረታቸው 0.03 ሚሊ ሜትርና ከዚያ በታች ሆነው በስብሰው ከአፈር ጋር የማይዋሃዱ የፕላስቲክ ምርቶችን ተለይቶ ለተገለፀ አገልግሎት በቀር ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም በአገር ውስጥ እንዳይመረቱ ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትል በማድረግ ዘገባ አላዘጋጀም፤ ባደረጋቸው የክትትል ስራዎች ከህግ ውጪ ሰርተው በተገኙ ድርጅቶች ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እርምጃ እንዲወሰድ አላደረገም።
- ባለስልጣኑ የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ የፕላስቲክ ምርቶችን የሚያመርቱ አምራቾች ያመረትዋቸው ምርቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ የሚሰበስቡበትና መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ወይም ምርቶቻቸው ተጠቃሚው ከተገለገለበት በኃላ ለሚያስከትሉት ብክለት ማካካሻ የሚሆን ክፍያ የሚከፍሉበትን እንዲሁም በጊዜ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ምርቱን የሚያቋርጡበትን እና በሌሎች ተተኪ ምርቶች የሚለውጡበትን አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡

- ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት በተመለከተ ከዘርፉ መ/ቤቶች፣ ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም ፤የከተማ አስተዳደሮች እና ክልሎች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህግ ተከባሪነት ደረጃን የሚገልፅ የቁጥጥርና ክትትል ሪፖርት መዘጋጀቱን ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ አላደረገም።
- ባለስልጣኑ ቆሻሻ በየቦታው እንዳይዝረከረክ እና ቆሻሻን መልሶ መጠቀም ላይ በሚፈለገው መጠን እንዲሰራ ለማድረግ እንዲቻል የከተማ አስተዳደሮች በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት መስክ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውን ክትትልና ድጋፍ አላደረገም።
- ባለስልጣኑ የባለሙያዎችን አቅም መገንባትና ማጎልበት እንዲቻል እና የሚመለከታቸው ተግባሪ አካላት ስለ ዘርፉ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት በተመለከተ ለዘርፉ መ/ቤቶች፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ተከታታይነት ባለው መልኩ ስልጠና አልሰጠም፤፡
- ባለስልጣኑ በደረቅ ቆሻሻና ፕላስቲክ ምርቶች ዙሪያ የተሻለ ለውጥ እንዲመጣና እና ሃገሪቱ የተቀናጀና የተደራጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እንዲኖራት ለማድረግ በደረቅ ቆሻሻና ፕላስቲክ ምርቶች ዙሪያ ዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን በመውሰድ ተግባራዊ አላደረገም

የሚሉ ናቸው፡፡

ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶችና ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል ይረዳሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል ቀርቧል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

114. የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የፕላስቲክ ምርቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነትን አካባቢ በማይጎዳ መልኩ ውጤታማነትን በተመለከተ ያለውን አሰራር ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ፤ እና ውጤታማ እንዲሁም አካባቢ እንዳይጎዳ ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዲተገበር ያስችላሉ ተብሎ የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ባለስልጣኑ በረቂቅ ደረጃ ያዘጋጃቸውን በ1989 ዓ.ም የወጣውን የአካባቢ ፖሊሲን ማሻሻያ እና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999 ማሻሻያ በሚመለከታቸው አካላት እንዲፀድቁ ክትትል በማድረግ ማፀደቅ አለበት፤ ተሻሽሎ የሚወጣውን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ደንቦች እና መመሪያዎች በቶሎ በማዘጋጀት እና ክትትል አድርጎ በማፀደቅ የህግ ማዕቀፎችን ሊያዘጋጅና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ በማድረግ ለስራ አፈፃፀም ትግበራ ምቹ ማድረግ አለበት፡፡
- ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህጎችና ደረጃዎች ተፈጻሚነት ላይ ያሉ ችግሮችን በመለየት የቁጥጥር ዘርፉን ለማሳደግና ለማፋጠን የሚረዳ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል በመቅረፅ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዙሪያ ፈንድ የሚያገኙበትን አማራጮችን በማፈላለግና ተግባራዊ በማድረግ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ሊወጣ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በአገሪቱ ያሉ ሁሉንም በደረቅ ቆሻሻ ስርዓት የገቡ ከተሞችን ለይቶ በማወቅ የከተማ አስተዳደሮች ዝቅተኛውን የአስተዳደር እርከናቸውንና የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ ባሳተፈ መልኩ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ስለማዘጋጀታቸውና በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ የቆሻሻ አሰባሰብን በተመለከተ ኃላፊነትን በባለቤትነት በመውሰድ መስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ የሚሰጡ አገልግሎቶች (የቆሻሻ አሰባሰብ፣ የማጓጓዣ ጊዜና ምልልስ) ለሁሉም

የህብረተሰብ ክፍልች ተደራሽ  እና ቋሚ ስለመሆኑ ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ሊደርስ የሚችል ብክለትን የመከላከያ እርምጃ መወሰዱን ክትትል በማድረግ፡ ምልክት የተደረገባቸው ጉድፍ ማጠራቀሚያዎች በየጎዳናው ዳርና በሌሎች የሕዝብ ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲቀመጡ፤ቆሻሻ በሚሰበሰብበት ወቅት ቢያንስ 2 የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ማለትም የሚበሰብስ እና ሊበሰብስ የማይችል ቆሻሻን ማጠራቀም የሚያስችል የተለያየ ከለር ባለው ገንዳ እየተከማቸ ስለመሆኑ፤ የጉድፍ ማጠራቀሚያ ሞልቶ ሳይዝረከረክ ቆሻሻ በየወቅቱ በቆሻሻ ሰብሳቢ ተሸከርካሪዎች መነሳቱን  ማረጋገጣቸውን እና ዘመናዊ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ስለማዘጋጀታቸው ክትትል እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል::
- ባለስልጣኑ በመስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ የሚገኙ በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ስራ ላይ ለተሰማሩ የራስ ጤንነትና ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች እንዲሁም የስራ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ ለሰራተኞች የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ስለመኖራቸው ክትትል በማድረግ የሚሰጠውን ግረመልስ ለተግባሪው አካል (ከተሞች) መድረሱን እና ተግባራዊ መደረጉን የሚከታተልበት አሰራር ሊኖረው ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ፕላስቲክ አምራቾችን እና የቆሻሻ ማከማቻ ላንድ ፊል ፕሮጀክቶች ጨምሮ ማንኛውም ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል የልማት ፕሮጀክቶት ባለቤት ወደ ትግበራ ከመግባቱ በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ በማካሄድ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ፈቃድ አግኝቶ ወደ ስራ እንዲገቡ ሊያደርግ እንዲሁም በተሰጣቸው ፈቃድ መሰረት መስራታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎች በማዘጋጀት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ  ቁጥጥር ላይ ወደ ፍትህ አካላት የሚቀርቡትን እና አስተዳደራዊ የሚወሰዳባቸውን ጉዳዮች ተለይተው ህጉን በተላለፉ አካላት ላይ ቅጣት እንዲፈፀም ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ቆሻሻን ጨምሮ የደረቅ ቆሻሻ የሚያደርሱት ጉዳት በአግባቡ በመረዳት የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ በተመለከተ ያለበትን ነባራዊ

ሁኔታ በጥናት እንዲለይ በማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚመለከታቸው አካባቢ አያያዝ ተግባሪ አካላት እና ህብረተሰቡ ተደራሽ በሆነ መልኩ ግንዛቤ መፍጠር አለበት፡፡


- ባለስልጣኑ ፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች ክትትል በዓመታዊ እቅዱ ላይ በማካተት ፕላስቲክ አምራች ድርጅቶችን አዋጁ ላይ በተቀመጠው ህግ መሰረት ማምረታቸውን እንዲሁም ከውጭ አገር ለሚገቡ የፕላስቲክ ምርቶች ተለይተው ለተፈቀዱ ምርቶች ብቻ መግባታቸውን ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትል አድርጎ ዘገባ በማዘጋጀት ህግን በተላለፉት ላይ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ የፕላስቲክ  ምርቶችን የሚያመርቱ አምራቾች ያመረትዋቸው ምርቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ የሚሰበስቡበትና መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ወይም ምርቶቻቸው ተጠቃሚው ከተገለገለበት በኃላ ለሚያስከትሉት ብክለት ማካካሻ የሚሆን ክፍያ የሚከፍሉበትን እንዲሁም በጊዜ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ምርቱን የሚያቋርጡበትን እና በሌሎች ተተኪ ምርቶች የሚለውጡበትን አሰራር በህግ ማዕቀፍ እንዲደገፉ በማድረግ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እንዲሁም የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ቅንጅታዊ አሰራሩን ሊያጠናክር እንዲሁም የከተማ አስተዳደሮች እና ክልሎች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህግ ተከባሪነት ደረጃን የሚገልፅ የቁጥጥርና ክትትል ሪፖርት መዘጋጀቱን ሊከታተል ፣ ሊቆጣጠር እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ ወደ ሀብትነት ለመቀየር የከተማ አስተዳደሮች በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት መስክ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ ኃላፊነቱን በአግባቡ በመወጣት የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት በተመለከተ ለዘርፉ መ/ቤቶች፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ተከታታይነት ባለው መልኩ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል።

- ባለስልጣኑ መልካም ተሞክሮ እንዲቀስሙ የላካቸውን ኃላፊዎች/ባለሙያዎች የወሰዱትን ተሞክሮዎች ለመተግበር የሚያስችል አሰራር እንዲኖር በማድረግ በደረቅ ቆሻሻና ፕላስቲክ ምርቶች ዙሪያ ዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮችን ወደ ታች/ተግባሪ አካላት ጋር በማውረድ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የበላይ ሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም መረጃ የሰበሰብንባቸው የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ- 1

### የአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ተቋማዊ መዋቅር



አባሪ 2

**የመመዘኛ መስፈርት** (Evaluative Criteria)

**የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡- የኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን**

**የኦዲቱ አካባቢ፡- የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የፕላስቲክ ምርቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነትን መገምገም፡፡**

| **የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች**(Audit Issues) | **የመመዘኛ መስፈርቶች** (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1. ባለስልጣኑ በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል ህግና ስርዓት በማዘጋጀት ተግባራዊ ስለማድረጉ መገምገም፡፡ | 1. ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999 በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ደንቦች እና መመሪያዎች በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999 አንቀፅ 18 |
| | 2. ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህጎችና ደረጃዎች ተፈጻሚነት የቁጥጥር ዘርፉን ለማሳደግና ለማፋጠን የሚረዳ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል እንዲቀረፅ ድጋፍ ሊያደርግና ድጋፉም ሲገኝ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** የደረቅ እና አደገኛ ቆሻሻ ህግ ተከባሪነት ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት |
| | 3. ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ሥርዓት ተከባሪነት ላይ ያሉ ችግሮች ጥናቶች እንዲካሄዱ ውጤቶችም እንዲተዋወቁ መድረኮችን ሊያመቻችና አፈጻጸሙን ሊገመግም ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** የደረቅ እና አደገኛ ቆሻሻ ህግ ተከባሪነት ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት |
| | 4. ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ የአካባቢ ብክለት ህግ ተከባሪነት ክትትል እና ቁጥጥር ስርዓት ሊያናጉ የሚችሉ ድርጊቶችና አካሄዶች አስቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ፣ ሲፈቀድ ተግባር ላይ ሊያውል ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** የደረቅ እና አደገኛ ቆሻሻ ህግ ተከባሪነት ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት እና ህግ ተከባሪነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተግባር እና ኃላፊነት |
| | 5. ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ቆሻሻ በአካባቢ፣ በሰው እና በእንስሳት የሚያደርሰውን ጉዳት በተመለከተ ጥናት ሊያደርግ እና በጥናቱ መሰረት ተገቢውን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** መልካም ተሞክሮ |

| የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች(Audit Issues) | የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | 6. ማንኛውም ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል የልማት ፕሮጀክቶት ባለቤት ወደ ትግበራ ከመግባቱ በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ በማካሄድ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ፈቃድ ሊያገኝ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 |
| | 7. ባለስልጣኑ በሚመለከታቸው የዘርፍ መ/ቤቶች የተሰጡ የአካባቢና የማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ የይሁንታ ፈቃዶች በህጉ መሠረት እየተገበሩ መሆናቸውን ሊያረጋገጥ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-**የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ ገፅ 36 |
| | 8. ባለስልጣኑ በጥናት የተለዩ የአካባቢ ችግሮች በስራ ላይ ባሉ ህጎች መቀረፋቸው እና አዲስ በሚወጡ ህጎች መሰረት ሊወገዱ የሚችሉበት አሰራር እንዲኖር በማድረግ፣ ውጤቱም ለሚመለከታቸው እንዲደርስ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-**የአካባቢ ህግ ተከባርነት ክትትል እና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ኃላፊነት |
| 2. **የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ ቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነትን መገምገም፡፡** | 9. ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ዝቅተኛውን የአስተዳደር እርከናቸውንና የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ ባሳተፈ መልኩ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀታቸውንና ተግባራዊ ማድረጋቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል:: **ምንጭ፡-** የደረቅ ቆሻሻ አዋጅ ቁጥር 513/2007 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ1 እና 4ሀ |
| | 10.ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ሊደርስ የሚችል ብክለትን የመከላከያ እርምጃ መወሰዱን ክትትል ሊያደርግ ይገባል:: **ምንጭ፡-** የደረቅ ቆሻሻ አዋጅ ቁጥር 513/2007 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 4ሠ |
| | 11.ባለሥልጣኑ በመስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ የቆሻሻ አሰባሰብ፣ የማጓጓዣ ጊዜና ምልልስ ለሁለም የህብረተሰብ ክፍልች ተደራሽ እና ቋሚ ስለመሆኑ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-**መልካም ተሞክሮ |

| የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች(Audit Issues) | የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
| --- | --- |
| | 12.ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች ምልክት የተደረገባቸው ጉድፍ ማጠራቀሚያዎች በየጎዳናው ዳርና በሌሎች የሕዝብ ማዘውተሪያ ስፍራዎች መቀመጥቸውን የሚረጋግጡ መሆኑን ክትትል ሊያደርግ ይገባል:: **ምንጭ፡-** የደረቅ ቆሻሻ አዋጅ ቁጥር 513/2007 አንቀፅ 5 ነዑስ አንቀፅስ 4ለ |
| | 13.ባለሥልጣኑ ቆሻሻ በሚሰበሰብበት ወቅት ቢያንስ 2 የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ማለትም የሚበሰብስ እና ሊበሰብስ የማይችል ቆሻሻን ማጠራቀም የሚያስችል የተለያየ ከለር ባለው ገንዳ እየተከማቸ ስለመሆኑ በመስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** ከመልካም ተሞክሮ |
| | 14.ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች የጉድፍ ማጠራቀሚያ ሞልቶ ሳይዝረከረክ ቆሻሻ በየወቅቱ መነሳቱን ማረጋገጣቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** የደረቅ ቆሻሻ አዋጅ ቁጥር 513/2007 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅስ 4ሐ |
| | 15.በመስተዳድሮች፣ ክልሎችና ከተሞች /ማዘጋጃ ቤቶች/ የሚገኙ በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ስራ ላይ ለተሰማሩ የራስ ጤንነትና ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች እንዱሁም የስራ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥና ወጪን ለመቀነስ ለሰራተኞች የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ስለመኖራቸው ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-**መልካም ተሞክሮ |
| | 16.ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች እና ክልሎች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህግ ተከባሪነት ደረጃን የሚገልፅ የቁጥጥርና ክትትል ሪፖርት መዘጋጀቱን ሊከታተል ፣ ሊቆጣጠር እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** የደረቅ እና አደገኛ ቆሻሻ ህግ ተከባሪነት ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት |
| | 17.ባለስልጣኑ ውፍረታቸው 0.03 ሚሊ ሜትርና ከዚያ በታች ሆነው በስብሰው ከአፈር ጋር የማይዋሃዱ የፕላስቲክ ከረጢቶችን ተለይቶ ለተገለፀ አገልግሎት በቀር ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም በአገር ውስጥ እንዳይመረቱ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** የደረቅ ቆሻሻ አዋጅ ቁጥር 513/2007 አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 2 ና |

| የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች(Audit Issues) | የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | 3 |
| | 18.ባለስልጣኑ የፕላስቲክ አምራች ተቋማት ላይ የክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ዘገባ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ ገፅ 31 |
| | 19.ባለስልጣኑ የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ የፕላስቲክ ምርቶችን የሚያመርቱ አምራቾች በጊዜ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ምርቱን የሚያቋርጡበትን እና በሌሎች ተተኪ ምርቶች የሚለውጡበትን አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** መልካም ተሞክሮ |
| | 20.ባለስልጣኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ቁጥጥር ላይ የተሰሩ ዘገባዎችን በመመርመር፣ ወደ ፍትህ አካላት የሚቀርቡትንና አስተዳደራዊ እርምት የሚወሰዳባቸው ጉዳዮች ላይ ሊወስን፣ ተግባራዊነቱን ሊከታተል፣ ሊደግፍ፣ ሊመራና ሊያስተዳድር ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** የደረቅ እና አደገኛ ቆሻሻ ህግ ተከባሪነት ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት |
| | 21.ባለሥልጣኑ ከተሞች በከተሞች አካባቢን የሚበክል አካል ተመጣጣኝ ክፍያ እንዲከፍል የማድረግና ጉልህ አሉታዊ ተጽዕኖ በሚያደርሱት ላይ ተጠያቂነትን በማስፈን አገልግሎቱ የራሱን ወጪ ሙሉ በሙሉ እንዲሸፍን የሚያደርግ ስርአት በመዘርጋት እየተገበሩ ስለመሆናቸው ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** የደረቅ ቆሻሻ አዋጅ ቁጥር 513/2007 አንቀፅ 17 ነዑስ አንቀፅ 4 እና ከመልካም ተሞክሮ |
| 3. **ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ** ፣ | 22.ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት በተመለከተ ከዘርፉ መ/ቤቶች፣ ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል። 16 **ምንጭ፡-** የተስተካከለው የ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ ገፅ-36 |

| **የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች**(Audit Issues) | ***የመመዘኛ መስፈርቶች*** (Evaluative Criteria) |
| --- | --- |
| **አጓጓዝ፣ አወጋገድ በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ውጤታማ መሆኑን መገምገም፡፡** | 23.ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት መስክ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል::ብቸኛ<br>**ምንጭ**፡- የደረቅ ቆሻሻ አዋጅ ቁጥር 513/2007 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅስ 1 |
| | 24. ባለስልጣኑ የፕላስቲክ አምራች ተቋማት ያመረትዋቸው ምርቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ ሚሰበሰቡበትና መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉበት አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ መደረጉን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** ከመልካም ተሞክሮ |
| | 25.ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፣አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት በተመለከተ ለዘርፉ መ/ቤቶች፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** የተስተካከለው የ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ ገፅ-36 |
| | 26.የፕላስቲክ ምርቶች በአካባቢ፣በሰው እና በእንስሳት የሚያደርሰው ጉዳት በተመለከተ በባለስልጣኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ**፡ መልካም ተሞክሮ |
| | 27.ባለስልጣኑ የከተማ አስተዳደሮች የአካባቢ ግንዛቤ ማስፋፊያ ተግባራትን ማቀዳቸውን እና መተግበራቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል::<br>**ምንጭ**፡- የደረቅ ቆሻሻ አዋጅ ቁጥር 513/2007 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 4መ |
| | 28.ባለስልጣኑ በደረቅ ቆሻሻና ፕላስቲክ ምርቶች ዙሪያ ዓለምአቀፍ መልካም ተሞክሮችን በመውሰድ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** መልካም ተሞክሮ |

አባሪ 3

## በዝርዝር ኦዲቱ ወቅት የተዳሰሱ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት

**<u>የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች</u>**

1. ኦሮሚያ ብ/ክ መንግስት የአካባቢ ጥበቃ ባስልጣን፣
2. ሃረሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣
3. ሲዳማ ብ/ክ/መንግስት የአካባቢ የደንና የአየር ለውጥ ባለስልጣን፣
4. የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ባስልጣን፣
5. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን
6. የምዕራብ ሃረርጌ ዞን ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣
7. ሻሸመኔ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣
8. አዳማ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣
9. ለሞጆ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣
10. የአቃቂ ቃሊቲ የአካባቢ ጥበቃ ፅ/ቤት
11. የአዲስ ክፍለ ከተማ የአካባ ጥበቃ ፅ/ቤት

**<u>የፅዳት አስተዳደር ጽ/ቤቶች</u>**

1. የአዲስ አበባ ከተማ የፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ
2. አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የፅዳት አስተዳደር ጽ/ቤት
3. አዲስ ከተማ የፅዳት አስተዳደር ፅ/ቤት
4. የድሬዳዋ ከተማ ፅዳትና ውበት አስተዳደር ኤጀንሲ፣
5. ሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር የከተማ ፅዳትና አረንጓዴ ልማት፣

**<u>ከተሞች (ማዘጋጀ ቤቶች)</u>**

1. የሃረሪ ማዘጋጃ ቤት፣
2. ሲዳማ ብ/ክ/መንግስት ሃዋሳ ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት፣
3. የጭሮ ከተማ ማዘጋጃ ቤት፣
4. አዳማ ማዘጋጃ ቤት፣
5. ለሞጆ ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት፣

**<u>የፕላስቲክ አምራች ድርጅቶች</u>**

1. ሞብላኮ ፕላስቲክ አምራች
2. ፒፒ ፕላስቲክ ማምረቻ
3. ሳራ ፍትዊ ፕላስቲክ ማምረቻ
4. ሚኪያስ ፕላስቲክ ፋብሪካ

5. አብዳልአዚዝ የፕላስቲክ ውጤቶች ኃ/የተ/የግል ማህበር
6. ቤስት የፕላስቲክ ማምረቻ
7. ዩኒክ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ ማህበር
8. ሙሉጌታ ፕላስቲክ ፋብሪካ
9. ጀማል አወል ፕላስቲክ ኢንዳስትሪ

**<u>የውሃ አምራች ድርጅት</u>**

1. የስ የውሃ ፋብሪካ
2. አኳአዲስ የውሃ ፋብሪካ

**<u>ሌሎች ባለድርሻ አካላት</u>**

1. ኢንዳስትሪ ሚኒስቴር
2. የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር
3. የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ

## አባሪ- 4 የደረቅና አደገኛ ቆሻሻ ህግ ተከባሪነት ዳ/ሬት የስራ ሂዳት ስዕላዊ መግለጫ፡-

